Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ

**1ኛ ክፍል**



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

1ኛ ክፍል


### አዘጋጆች

ትሰፋሚካኤል ያየህ

በኃይሉ ዘለቀ

ርብቃ ወንድምአገኝ

### ገምጋሚዎች

ኢየሩሳሌም በዳኔ

ማርቆስ ወልደሃና

ሰሎሞን ኃይለማርያም

### አስባተባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

### ሌይአውት ዲዛይን

በእንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም / 2021 /

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

© 2014ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት የተጠቀምንባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን።

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

# ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽኃፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽኃፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

# ማውጫ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


የመጽሐፉ መግቢያ....iv

**ምዕራፍ 1. ጥበባዊ ግንዛቤ....1**

የምዕራፍ አንድ መግቢያ....1

1.1. በምስል የተቀረፁ ቀላል ዜማዎችን ማዳመጥና መመልከት፡-....2

በየዕለቱ የምንሰማቸው መዝሙሮች....2

1.2 ውዝዋዜ....8

1.3 በቪዲዮ የተቀረፁ ፊልሞችን አይቶ ድርጊታቸውን መናገር....10

ፊልም....11

1.3.1ድርጊቶችን እና መልዕክቶችን መለየት....14

1 ድርጊቶች....14

2 መልዕክቶች....16

1.4ምስሎችን መለየት....17

ማጠቃለያና የማጠቃለያ ጥያቄዎች....20

**ምዕራፍ 2. ፈጠራን መግለፅ....22**

የምዕራፍ ሁለት መግቢያ....22

2.1. የቤተሰብ መዝሙር መዘመር....23

2.2 በቀላል ምቶች መወዛወዝ....28

2.3 የቤተሰብን ሚና መቅዳት....32

ቤተሰብ ምንድ ነው?....32

2.4. መስመር መሞነጫጨርን መለማመድ፣ መስመር መሳልና  መቀባት፡፡....37

መስመር ምንድነው?....37

ማጠቃለያ....42

የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች....43

ምዕራፍ 3. ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች....44

የምዕራፍ ሦስት መግቢያ....44

3. ባህል....44

3.1. በአካባቢውና በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ መዝሙራት....45

3.2 በአከባቢውና በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ውዝዋዜዎች....54

3.3 ተረቶች ፣ ትረካዎች ፣ እንቆቅልሽ ጫወታዎች....57
3.4. በአካባቢያችን ያሉ ቀለማት....62
ማጠቃለያ....67

**ምዕራፍ 4. ሥነ-ውበታዊ እሴት....68**
የምዕራፍ አራትመግቢያ....68
4. ባህላዊ ልምዶችን ማድነቅ....69
4.1 የቤተሰብ መዝሙር....70
4.2 ውዝዋዜ....78
4.3 የልጆች ባህላዊ ጨዋታ ልማዶችን ማድነቅ....80
4.4. ባህላዊ ልምዶችን በምስል ማድነቅ....86
ባህላዊ ልምዶች ከዕይታ ጥበብ ጋር....88
ባህላዊ ድርጊቶች የሚሰጡትን ጠቀሜታ በጥቂቱ....90
ማጠቃለያ....94

**ምዕራፍ 5.ጥመርታ ዝምድና እና ትግበራ....95**
የምዕራፍ አምስት መግቢያ....95
5.1. የቡድን ዝማሬ....97
አተገባበር ማለት ምን ማለት ነው?....97
5.2 በቡድን ውዝዋዜ....103
ውዝዋዜ እና ተፈጥሮ....103
5.3 የሚና ጨዋታ በቡድን ውስጥ....105
5.4 የክወናና የዕይታ ጥበብ ጥመርታ፤ ዝምድናና ትግበራ ....108
ማጠቃለያ....114
ዋቢ መፅሃፎች....115

# መግቢያ

የክወና እና የዕይታ ጥበባት ትምህርት ማለት የሙዚቃ ጥበብ፤የውዝዋዜ ጥበብ፣ የትያትር ጥበብ እና የስዕል ጥበብ ትምህርቶች ቅንጅት ነው፡፡

ይህ መማሪያ ማስተማሪያ መፅሐፍ የተዘጋጀው ተሸሽሎ በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ የክ.ዕ.ጥበብ ለአንድ ሃገር ሕዝብ የሚሰጠው ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ በመማርና ማስተማር ሂደት ውስጥ ለማህበረሰቡ ዕድገት የሚያደርገው አስተዋፅኦም እጅግ የላቀ ነው፡፡

ይህ መፅሐፍ በአምስት ክፍለ ትምህርቶች የተከፈለ ነው፡አላማው አራቱንም የክወና እና የዕይታ ጥበባት ትምህርቶች ንድፈ ሀሳብን፤ ታሪካዊና ባህላዊ (ሥነ-ውበታዊ)እሴትን ማድነቅ እንዲችሉና የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርትን ተማሪዎች እንዲማሩበትና፤በሃገራቸው የሚገኙትን የክወናና የዕይታ ጥበባትን እንዲረዱ የሃገራቸውን የጥበብ ስራዎችን እንዲያደንቁና ለባህል እድገትም ይህ የተማሪው መፅሀፍ መምሪያ የበኩሉን ድርሻ እንደሚያበረክት ከትምህርት ፖሊሲና ሥልጠና ዓላማ አኳያ የታሰበለትን ግብ እንዲመታ ነው፡፡

ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት፡-

ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የሚከተሉትን ትችላላችሁ፡፡

- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ድምፆችን፣ ትለያላችሁ፡፡
- መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፤ሙዚቃዊ ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ፡፡
- በአከባቢያችን የሚገኙትን ጥበባት ትረዳላችሁ፡፡
- የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ጥበባዊ ግንዛቤ

### መግቢያ

ጥበባዊ ግንዛቤማጤን ማለት፡-ስለምናውቀውም ሆነ ስለማናውቀው ነገር መመርመር፤ማስተዋል፤መረዳት ማለት ነው፡፡ነገሮችን መርምሮ ማወቅ ማለት ክፉውን፤ደጉን፤መልካሙንና መጥፎውን ለይቶ መረዳት አስተውሎ መገንዘብ ማወቅ ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ማጤን ማለት የአንድን ነገር ባህሪ፤ተፈጥሮ አስፈላጊነቱን መርምሮ የመረዳት ጥበብ ማለት ነው፡፡

የዚህ ትምህርት ዓላማ የአንድን ነገር ባህሪ፤ተፈጥሮ አስፈላጊነቱን መርምረን መረዳት እንድትችሉ ነው፡፡

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት፡-

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች የሚከተሉትን ትችላላችሁ፡፡

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ድምፆችን፣ትለያላችሁ፡፡
- መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፤ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ፡፡
- በአከባቢያችን የሚገኙትን ጥበባት ትረዳላችሁ፡፡
- የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ፡፡

## 1.1. በምስል የተቀረፁ ቀላል ዜማዎችን ማዳመጥና መመልከት:-

ከዚህ ርዕስ በኋላ ዝርዝር የመማር ውጤት።ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ።

- የየዕለት የዝማሬ ልምምዳችሁን ታዳብራላችሁ።
- የቋንቋ እድገታችሁን እና የትምህርት ዝግጁነታችሁን ትጨምራላችሁ።
- የግል ንፅህናችሁን መጠበቅ ጤናን መጠበቅ እንደሆነ ትማራላችሁ።
- በአከባቢ የሚገኙትን የጥበብ ስራዎችን ትረዳላችሁ።

### በየዕለቱ የምንሰማቸው መዝሙሮች

በሰፈራችን፤በቤታችን ውስጥ ወላጆቻችን ታላላቅ ወንድሞቻችን፤እህቶቻችን፣በትምህርትመምህራኖቻችን የሚዘምሩልን ለዓይናችን ፤ለጆሯችን አዲስ ያልሆኑ በምስል ወይንም በድምፅ ተቀርፀው የሚቀርቡ ናቸው። በሙዚቃ ታጅበው ጥበባዊ በሆነ መንገድ አምረው በቴሌቪዥን በልጆች ፕሮግራም ጊዜ በየዕለቱ የምናያቸው የምንሰማቸው ናቸው። በተለያዩ የአካል እንቅስቃሴ የሚገለፁ ናቸው።

ለምሳሌ:- በመዝለል፣በመሮጥ በመቀመጥ፣ በመነሳት፣ ዓይንን በመጨፈን እጅ ለእጅ በመያያዝ፣ክብ ሰርቶ በመቀመጥ

በመቆም፤በመስመር በመደርደር ወዘተ... የምንጫወታቸው ናቸው፡፡

ቀላል መዝሙሮች

መዝሙር 1.ጤንነቴን እጠብቃለሁ

ጤና ማለት የተሟላ አካላችንና፤ዓዕምሯችን ደህና ሲሆን ነው፡፡

የግል ንፅህናችንን የተጠበቀ ሲሆን የአካላችንም፤የዓዕምሯችንም ጤንነት ይጠበቃል፡፡ ስለ ጤና እየዘምርን እንቅስቃሴ ማድረግ ዋና ተግባራችን መሆን አለበት፡፡

ጤንነቴን እጠብቃለሁ

ላ ላ ላ ላላ ላላ ላ ላ ላ ላ ላ ላ ላ ላ

ንፅህናዬን እጠብቃለሁ ሁልጊዜ እጠነቀቃለሁ
እጆቼንም እታጠባለሁ ጤንነቴን
እጠብቃለሁ



## መዝሙር 2 . ወንድሜ ያዕቆብ

ወንድሜ ያዕቆብ ወንድሜ ያዕቆብ

ተኛህ ወይ ተኛህ ወይ

ደወል ተደወለ ደወል ተደወለ

ተነሳ ተነሳ.

## መዝሙር 3:- 10 አረንጓዴ ጠርሙሶች

ይህ መዝሙር ከ0-10 ያሉ ቁጥሮችን አዝናኝ በሆነ መንገድ መቀነስ የምንማርበት ጥበባዊ መንገድ ነው::



10..አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳው ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር 9.. ይቀራል።

9..አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳወ ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር 8.. ይቀራል።

8..አረንጓዴ.....ጠርሙሶች በግድግዳወ ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር 7.. ይቀራል።

7..አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳወ ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር 6.. ይቀራል።

6..አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳወ ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር 5..ይቀራል።

5..አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳወ ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር 4..ይቀራል።

4 አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳወ ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር 3..ይቀራል።

3 አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳወ ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር 2..ይቀራል።

2..አረንጓዴ.....ጠርሙሶች በግድግዳው ላይ ድንገት አንዱ
ወድቆ ቢሰበር 1..ይቀራል።

1..አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳው ላይ ድንገት አንዱ
ወድቆ ቢሰበር 0..ይቀራል....0..ይቀራል...0..ይቀራል።

መዝሙር 4.ሳይንስ ሳይንስ

ሳይንስ ሳይንስ መድሀኒቴ
ያስተማረኝ ጤንነቴን
ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን ስበላ
በህልሜ ታየኝ ሳይንስ ሳጠና
ሳይንስ ሳጠና ሳይንስ ሳጠና

ሳይንስ ሳይንስ መድሀኒቴ

ያስተማረኝ ጤንነቴን .........





## መዝሙር 5፦ ልጅነቴ ማርና ወተት

ይህ የመዝሙር ይዘት የጨዋታ መዝሙሮች ከሚባሉት ውስጥ የሚመደብ ሙዚቃዊ ጥበብ ነው።

የዚህ የመዝሙር ይዘት በሙዚቃ የሚታጀብ የጨዋታ ጥበብ ነው።

ሙዚቃዊ ጨዋታውን ለመጀመር ፊታችሁን ወደ ክቡ ውስጥ አዙራችሁ በመተቃቀፍ ትቆማላችሁ ።

አሁን በኮሮና ምክንያት መተቃቀፍ ስለማይኖር በያላችሁበት እራቅ እራቅ በማለት ትዘምራላችሁ።

## መዝሙር 6. አልፋ ቤት መዝሙር

ኤ ቢ ሲ ዲ ኢ ኤፍ ጂ ኤች አይ ጀ ኬ

A B C D E F G H I J K

ኤል ኤም ኤን ኦ ፒ ኪው አር ኤስ ቲ ዩ ቪ ደብሊው ኤክስ

L M N O P Q R S T U V W X

ዋይ ዜድ

Y Z

## 1.2 ውዝዋዜ

ከዚህ ርዕስ በኋላ ዝርዝር የመማር ውጤት፡-

- እየዘመራችሁ መወዛወዝን ትማራላችሁ፡፡
- ምትን ጠብቃችሁ በመዝሙሩ መወዛወዝ ትችላላችሁ፡፡
- በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ጥበባት ታደንቃላችሁ
- ሰውነታችሁን በማንቀሳቀስ እንቅስቃሴን ትማራላችሁ፡፡

ውዝዋዜ ሙዚቃዊ ምት ተከትሎ የሚደረግ የሰውነት እንቅስቃሴ ነው፡፡ ውዝዋዜ የሚወዛወዙ ሰዎች ተወዛዋዥ ይባላሉ፡፡ ከሙዚቃ ጋር መንቀሳቀስ ወይም መወዛወዝ ደስታን የሚሰጥ ጥበባዊ ክወና ነው፡፡ እናንተም ያያችሁትን ውዝዋዜን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡


## መዝሙር 1.ተነሱ እንጫወት

- ✓ ግጥሙ በሚያዘው መንገድ እንቅስቃሴ እያደረጋችሁ መዘመር ያስፈልጋል
- ✓ ስለሀገራችሁ የውዝዋዜ ጥበብ ታላላቆቻችሁን በመጠየቅ ለመምህራችሁ አስረዱ

ተነሱ እንጫወት አይገኝም ልጅነት

አማርኛ ብንጨፍር በያገራችን ባህል
እስክስ.........እስክስ........እስክስ
አዝማች
ኦሮምኛ ብንጨፍር በያገራችን ባህል
አሾ.....አሾ....አሾ
ተነሱ እንጫወት አይገኝም ልጅነት 2x
ትግርኛም ደስ ይለኛል
እንደዚ ያስብለኛል
ሳይ....ሳይ....ሳይ....ሳይ
ሳይ....ሳይ....ሳይ....ሳይ
ተነሱ እንጫወት አይገኝም ልጅነት 2x
ጉራጊኛም ደስ ይለኛል
እንደዚ ያስብለኛል
እዝዝ.....እዝዝ.....እዝዝ

..





## 1.3 በቪዲዮ የተቀረፁ ፊልሞችን አይቶ ድርጊታቸውን መናገር

ከዚህ ንዑስ ርእስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- ፊልም ከማየት ባለፈ ያያችሁትን መረዳት ትችላላችሁ
- ፊልም ለማየት የሚኖራችሁ ፍላጎት ከፍ ይላል፡፡
- በፊልም ያያችሁትን ነገር ማስረዳት ትችላላችሁ፡፡

## ፊልም

ፊልም ማለት በቴሌቪዥን ወይም በ እስክሪን የሚታዩ የተንቀሳቃሽ ምስሎች ስብስብ ማለት ነው፡፡



ለምሳሌ

ጢቆ እና ቢጢቆ (በ የኢትዮጲያ ልጆች ቴሌቪዥን)




ኢቶጲስ (በ E B S ቴሌቪዥን)



ጸሃይ መማር ትወዳለች (በ E B C ቴሌቪዥን)



ቶም እና ጄሪ



ሁለቱ ደቦሎች

## መልመጃ አንድ

1. ተማሪዎች፡- እናንተስ ምን አይነት ፊልም አይታችኋል?
2. አይታችሁ የወደዳችሁት ፊልም የቱ ነው?

## መልመጃ ሁለት

1. ፊልም ላይ ከምታዩአቸው ገጸባህሪያት እናንተ የምትወዱት የትኛውን ነው?
2. ፊልም በማየት ምን ተጠቀማችሁ?

## መልመጃ ሶስት

መምህር የሚያሳዩአችሁን ፊልም አይታችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ.

1. ምን እንዳያችሁ አስረዱ?
2. ምን መልዕክት አገኛችሁ?
3. የወደዳችሁትን ገጸባህሪ በድርጊት አሳዩ?

ከላይ የተጠቀሱትን ፊልሞች እያዩ መዝናናት ብቻ ሳይሆን ምን ምን መልእክት ተላለፈ፣ ማን ምን ተናገረ፣ እንዴት ሆኖ ተናገረ፣ ምን አይነት አለባበስ ለበሷል፣ አኔ የተኛው ገጸባህሪ አስደሰተኝ፣ ለምን አስደሰተኝ ወዘተ የመሳሰሉትን ጉዳዮች ማጤን እና መለማመድ ያስፈልጋል፡፡

## 1.3.1 ድርጊቶችን እና መልዕክቶችን መለየት

ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ

- የሰዎችን የየዕለት ድርጊቶችን ለይታችሁ ታውቃላችሁ፡፡
- በሰዎች መካከል ያለውን ማህበራዊ ሕይወት ትረዳላችሁ፡፡
- አካባቢያችሁን ታስተውላላችሁ፡፡
- በየዕለቱ የምታዩትን እና የምትሰሙትን መልዕክት ታስተውላላችሁ፡፡
- ከምታዩት የሰዎች ድርጊቶች ውስጥ ለእናንተ የሚመጥነውን መለማመድ ትችላላችሁ፡፡

### 1. ድርጊቶች

ድርጊት ማለት ሰዎች ከሰው ጋር ወይም ለብቻቸው ሆነው የሚሰሩት ስራ ወይም የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ማለት ነው





ለምሳሌ፡- ሰላምታ መለዋወጥ .የልጆች ጨዋታ

ምግብ ማብሰል

ልብስ ማጠብ





ሌሎች ድርጊቶች ደግሞ

- የገበያ እንቅስቃሴ፤ቤት ማፅዳት፤ለቅሶ መድረስ
- ድግስ መደገስ፤ልደት ማክበር ወዘተ....ናቸው።

ታዲያ እናንተም የሰዎችን ድርጊቶች በደንብ ማየት አለባችሁ ምክንያቱም የትወና ሙያ የሚጀምረው ከዚህ ነው።

### መልመጃ አንድ

1. ከላይ ከተዘረዘሩት ሌላ ምን አይነት ድርጊት ታውቃላችሁ
2. ከምታዩአቸው ድርጊቶች ምን ትረዳላችሁ
3. ለብቻ የሚደረጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው
4. ከሰው ጋር የሚደረጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው

## መልመጃ ሁለት

ከስር በምስል ከሚታዩት ድርጊቶች ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ ፡፡





1. መልዕክቶች

- መልዕክት ማለት ምን ማለት እንደሆን ታውቃላችሁ፡፡

1. የሆነ ምክር ወይም የሆነ ትምህርት በድራማ ወይም በጽሁፍ ወይም በሙዚቃ ሲተላለፍ መልዕክት ይባላል፡፡
2. መንገድ ላይ ከመኪና አደጋ ተጠንቀቁ ሲባል ከሰማችሁ መልዕክት ሰማችሁ ማለት ነው፡፡

## መልመጃ ሦስት

1. እናንተም የምታውቁትን የመልዕክት አይነት ለመምህራችሁ አስረዱ?
2. በቴሌቪዥን ወይም በሬዲዮ ሲተላለፍ የሰማችሁት መልዕክት ካለ አስረዱ?
3. መምህራን ከሚያስተላልፉት መልዕክቶች ውስጥ የምታስታወሱትን ተናገሩ?

## 1.4 ምስሎችን መለየት

ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- አካባቢያችሁን በሚገባ መቃኘት ትለምዳላችሁ
- ያያችሁትን ምስሎች ማስተዋል ትችላላችሁ
- አንዱ ምስል ከሌላው ምስል ያለውን ልዩነት ትገነዘባላችሁ
- ለምታዩት ነገር ትኩረት ማድረግን ትለምዳላችሁ

### ምስሎች

ምስሎች ማለት በፎቶ ወይም በስዕል ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ከሱቅ የምትገዟቸው የተለያዩ ጣፋጮች፣ ቁሳቁሶች፣ በመንገድ ላይ ስትሄዱ ሰዎች በተሰበሰቡበት ስፍራ በመጸዳጃ ቦታ፣ በትራንስፖርት ፣ቆሻሻ የምናስወግድበት ፣የመጽሐፍት ቤት ፣አካል ጉዳተኞች ባሉበት ቦታ፣ የተለያዩ ምስሎች ምን ማድረግ እንዳለበት ቃላትን ተክተው መልዕክት ያስተላልፉልናል።

በአካባቢያችን እነዚህ ምስሎች ልናጤናቸው ልንተገብራቸው ይገባል።

## መልመጃ አንድ

ከላይ የተሰጣችሁን ምሳሌ መሰረት በማድረግ በመንገድ ላይ የተመለከታችሁትን የተለያዩ ምስሎች ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

## ምስሎችን መለየት

ምስሎችን መለየት ማለት ከጠዋት እስከማታ ድረስ ባለው እንቅስቃሴአችሁ ውስጥ የምታዩአቸውን ምስሎች ማወቅ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡-





ሀ፡- በምትገለገሉበት የትምህርት ቤት መጸዳጃ የወንድና የሴት የምትለዩት እንዴት ነው

ለ፡- ቆሻሻን በአግባቡ የሚወገድበት መንገድ






ሐ፡- ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ማስክ ማድረግ



መ፡- አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ





## መልመጃ ሁለት

1. ከላይ የተቀመጡት ምስሎች የምን የምን ምስሎች እንደሆኑ አስረዱ
2. ከላይ የተቀመጡትን ምስሎች በደንብ አይታችሁ አንዱ ካንዱ ያለውን ልዩነት አስረዱ

## ማጠቃለያ

ተማሪዎች በምስል የተመለከቱትን የተለያዩ ሃሳቦችን ይሚገልፁ መዝሙሮች በመዘምር በአካባቢያችሁ፤ያሉምስሎችን፣ድርጊቶችንና መልዕክቶችን መለየት ችላችኋል፡፡

ያያችሁትን ነገር ማስተዋል ከቻላችሁ ለወደፊት የፈጠራ ችሎታችሁን ያዳብርላችኋል፡፡

በአካባቢያችሁ የምታዩትን ነገሮች ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

የተለያዩ በአካባቢያችሁ ያሉ የየዕለት ድርጊቶችን ለይታችሁ ማወቅ እንዳለባችሁ አይታችኋል፡፡ በሰዎች መካከል ያለውን ማህበራዊ አኗኗር ዘዴ መረዳት ችላችኋል፡፡ በየዕለቱ የምታዩትን እና የምትሰሙትን መልዕክት ማስተዋል እንደሚገባችሁ አውቀችኋል፡፡ ስለዚህ የአንድን ነገር ተፈጥሯዊ ባህሪ እና የሰዎችን ድርጊቶች ለእናንተ በሚመጥን መልኩ ማጤን እና ማስተዋል ትችላላችሁ ማለት ነው፡፡

## የማጠቃለያ ምዘና

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. በክፍል ውስጥ ስትዘምሩት ከነበሩ መዝሙሮች አንዱን ለየብቻ እየዘመራችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

2. ሳይንስ ሳይንስ የሚለው መዝሙር ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?

3. በየቀኑ የምናየው ድርጊት የቱ እንደሆነ ምረጡ፡፡

ሀ. ድመት ለ. ኳስ ሐ. ሰላምታ ልውውጥ መ. የእንስሳት ምስል

4. ፊልም የሚታየው በ ሬዲዮ ነው

ሀ. እውነት ለ. ሐሰት

# ምዕራፍ ሁለት

## ፈጠራን መግለፅ

### መግቢያ

ፈጠራን መግለፅ ማለት ስለ አንድ የግል ግኝታችን ስለሆነ ነገር ሙዚቃም ሊሆን ይችላል አዲስ ያወቅነውን እውቀት በመረጃና በማስረጃ የተረጋገጠን ተሞክሮና ልምድን የራሳችን የሆነ የፈጠራ ስራን ለሌሎች ሰዎች መግለፅ፣ መንገር፣ ማሳወቅ፣ማስተማር እና ለቤተሰቦቻችን፣ ለመምህሮቻችን፣ ለጓደኞቻችን ሃሳባችንንና ጥያቄዎቻችንን በነፃነት መንገርና መጠየቅ ማለት ነው፡፡

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ፡፡

- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ድምፆች ትለያላችሁ፡፡
- የቤተሰብ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፡፡
- በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ጥበባት ትረዳላችሁ፡፡
- የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ፡፡

## 2.1. የቤተሰብ መዝሙር መዘመር

በዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ ዝርዝር የመማር ውጤት

- ቀላል የቤተሰብ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ።
- በአከባቢያችሁ የሚገኙትን የጥበብ ስራዎች ታደንቃላችሁ።
- ዜማን፤ምትን፤ግጥም ጠብቃችሁ አስታውሳችሁ ትዘምራላችሁ።
- የቋንቋ እና የትምህርት ዝግጁነታችሁን ታሳድጋላችሁ።

የቤተሰብ መዝሙሮችን መዝሙር ስንል ቤተሰቦቻችን በጨወታ ጊዜ፤በመኝታ ጊዜ፤የሚዘምሩልን ቀለል ያሉ አስተማሪና አዝናኝ መልዕክቶችን የያዙ ስለ ቤተሰብ አባላት ፤ስለፍቅር፤ስለመከባበር የሚገልፁና፤የሚያስተምሩ መዝሙሮች በዜማና በግጥም ተውበው የሚቀርቡበት ሙዚቃዊ ጥበብ ነው።

## መዝሙር 1. እማዬ እና አባዬ እወዳችኋለሁ

የዚህ መዝሙር አጠቃላይ ሃሳቡ ፍቅራችሁን ለወላጆቻችሁ የምትገልፁበት፤ የወላጆቻችሁን ፍቅርም እንደሚያስፈልጋችሁ ለቤተሰቦቻችሁ የምትገልፁበት የቤተሰብ መዝሙር ጥበብነው።

እማዬ በጣም እወድሻለሁ

እማዬ በጣም እወድሻለሁ

ጎበዝ ልጅ ሆኜ አኮራሻለሁ

እቅፍ አድርገሽ ሳሚኝ....እማዬ በጣም እወድሻለሁ
አባዬ በጣም እወድሃለሁ አባዬ በጣም እወድሃለሁ
ጎበዝ ልጅ ሆኜ አኮራሃለሁ

እቅፍ አድርገህ ሳመኝ.....አባዬ በጣም እወድካለሁ





## መዝሙር 2. ስለ መከባበር መዘመር



- ልጆች ይህን መዝሙር ከመዘመራችን በፊት መልዕክቱ ምንእንደሆነ መምህራችሁ የሚነግሯችሁን፤የሚያነቡላችሁን በደንብ አዳምጡ፡፡
- ስለ መከባበር ታላላቆቻችሁን ጠይቃችሁ ሀሳባችሁን ለመምህርችሁ ይግለጹ፡፡

የዚህ መዝሙር አጠቃላይ ሃሳብ ስለ መከባበር ነው፡፡በቤት ውስት ቤተሰቦቻችንን በማክበር የሚያዙንን ነገሮች በአቅማችን መታዘዝ ፡፡

ከጓደኞቻችን ጋር በሰፈራችንም ሆነ በትምህርት ቤታችን ውስጥ ስንጫወት፤ስንማር በመተሳሰብ በመከባበር መሆን አለበት፡፡ አስተማሪዎቻችን የሚሰጡንን የቤት ስራ መስራትም መምህራችንን ማክበር ማለት ነው፡፡ በዕድሜ ከኛ የሚበልጡ

ትላልቅ ሰዎችን ማክበር፡፡

### መከባበር

ቤተሰቤን በጣም አከብራለሁ…ላላ ላላ

ጓደኞቼን በጣም አከብራለሁ…I LOVE YOU

አስተማሪዬን አከብራለሁ…ላላ ላላ

ሃገሬን በጣም እወዳለሁ I LOVE YOU ALL.






መልመጃ 1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. እማዬ በጣም እወድሻለሁ ----------------- አኮራሻለሁ

   ሀ.ሰነፍ ልጅ ሆኜ ለ. ጎበዝ ልጅ ሆኜ

2. እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1.መምህርን፤ወላጅን፤ጓደኛን ማክበር አያስፈልግም፡፡

   ሀ. እውነት ለ. ሐሰት

•የግል ፅብረቃ( የቃል ጥያቄ )

3. ከዘመራችኋቸው መዝሙሮች ውስጥ የአንዱን መዝሙር ሃሳብ ለመምህራችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ፡፡

   መልስ:----------------------------------

4. የወደዳችሁትን መዝሙር ለመምህራችሁ፤ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘምሩ፡፡

## 2.2 በቀላል ምቶች መወዛወዝ

ከዚህ ክፍል ትምህርት በኋላ የሚጠበቅ ዝርዝር የመማር ውጤት

ከዚህ የክፍል ደረጃ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ፡፡

- በአከባቢያችሁ የሚገኙትን የጥበብ ስራዎችታደንቃላችሁ፡፡
- ቀላል ምቶችን ጠብቃችሁ አስታውሳችሁ መወዛወዝ ትችላላችሁ፡፡
- የቋንቋ እና የትምህርት እድገታችሁን ትጨምራላችሁ፡፡

ውዝዋዜ በሰውነት እንቅስቃሴ የሚታጀብ፤ሚፈፀም ሙዚቃዊ ጥበብ ነው፡፡ የውዝዋዜ ጥበብ በሃዘን ጊዜ፤በደስታ ጊዜ የሚሰማንን ስሜት የምንገልጽበት ጥበብ ነው፡፡ታሪካችንን እና ባህላችንን ጥበባዊ በሆነ መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ የምናስተላልፍበት ጥበብ ነው፡፡

- ታላላቆቻችሁን በመጠየቅ የምታውቁትን እና የወደዳችሁትን የውዝዋዜ አይነት ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

ውዝዋዜ በግል ወይም በቡድን ሆነን የምንሰራውና የተሻለ ስሜት እንዲሰማን የሚያደርግ የክወናና የእይታ ጥበብ ነው። እጆቻችንን ወደ ቀኝ እና ወደ ግራ እያደረግን መዘመርና በመወዛወዝ መላ ሰውነታችንን በማንቀሳቀስ እየዘመርን በምስል በተደገፉ የሀገራችንን የተለይዩ የውዝዋዜ አይነቶች እንወዛወዛለን

## መልመጃ 1. ዳንስ

ቀኝ እጃችን ወደ ላይ...ቀኝ እጃችን ወደ ታች

ግራ እጃችን ወደ ታች ግራ እጃችን ወደ ላይ

ዳንስ...ዳንስ....ዳንስ...ዳንስ
ዳንስ.....ቸብ....ቸብ...ቁም

ወዝ....ወዝ.....ወዝ...ወዝ

ወዝ.....ቸብ....ቸብ....ቁም






- ✓ ተማሪዎች የመዝሙሩን መልዕክት ምን ማለት እንደሆን መምህራችሁ የሚጠይቋችሁን በመስማት መልሱ፡፡

## መልመጃ 2. ባህሌን አከብራለሁ

ሃገሬን እኔ እወዳታለሁ
ባህሌን በጣም አክብራለሁ
እስክስ እሰክስ እላለሁ

ወላይተኛ..... እጨፍራለሁ

ኦሮምኛ.... እጨፍራለሁ
አማርኛ..... እጨፍራለሁ
በትግረኛ...እጨፍራለሁ
ጉራግኛ.....እጨፍራለሁ





## መልመጃ 3 ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ

1. ከተመለከታችኋቸው ባህላዊ ውዝዋዜዎች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱን ጥቀሱ?

ሀ.--------------- ለ. -------------- ሐ. ------------------

2. ከዘመራችኋቸው መዝሙሮች ውስጥ የአንዱን መዝሙር ሃሳብ ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ታስረዳላችሁ ?

3. የወደዳችሁትን መዝሙር ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘምሩላቸው፡፡

## 2.3 የቤተሰብን ሚና መቅዳት

<u>ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት፡-</u>

- በስነምግባር ታንጾን እንድናድግ ቤተሰብ መሰረት መሆኑን ታወቃላችሁ
- ቀላል የቤተሰብ የትወና ጫዋታዎችን ትጫወታላችሁ
- የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን እየተመለከታችሁ መለማመድን ትማራላችሁ፡፡

**ቤተሰብ**



### ቤተሰብ ምንድን ነው?

ቤተሰብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከአስተማሪዎቻችን እና ከታላላቆቻቸው ጠይቀን መልሱን ለመምህራችን እንገልፃለን፡፡

የቤተሰብ ሚና መቅዳት ማለት ምን ማለት ነው ?

ተማሪዎች መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ።

**መልመጃ 1**

ቀጥሎ ያሉትን የቤተሰብ አባላትን ሁኔታ ተለማመዱ

- እንደ አባት ማውራት፣መናገር፣

ለምሳሌ 1

አባት፡- ልጄ ጎበዝ ተማሪ ከሆንክ እኔ ብቻ ሳልሆን ሁሉም ሰው ይኮራብሃል እሺ

ልጅ፡- እሺ አባቴ ጎብዝ ልጅ እሆናለሁ

አባት፡- ጎሽ የኔ ልጅ በርታ/ ደግሞ እናትህን አታስቸግር፣ ታላላቆችህን አክብር እሺ

ልጅ፡- እሺ አባቴ

አባት፡- በል አሁን ግባና የቤት ስራህን ስራና ስትጨርስ ያጠናኸውን እጠይቅሃለሁ

- እንደ እናት መናገር፤መስራት፤ቡና ማፍላት..ወዘተ

ለምሳሌ 2
እናት፡- እሰቲ የኔ ልጅ ጎረቤቶቻችንን ቡና ጥሪ
ልጅ፡- እሺ እማዬ
እናት፡- ቶሎ ኑ ቡናው ወጥቷል በያቸው ታዲያ
ልጅ፡- እሺ አሁኑኑ ቶሎ ኑ እላቸዋለሁ
እናት፡- ጎሽ የኔ ቆንጆ ልጅ አደጊልኝ

- እንደ ታላቅ ወንድም እና እነደ ታላቅ እህት መወያየት

ለምሳሌ 3
ወንድም፡- እህቴ
እህት፡- አቤት ወንድሜ
ወንድም፡- እናታችን የት ሄዳ ነው?
እህት፡- ጎረቤት ታሞ ልትጠይቅ ሄዳለች
ወንድም፡- አባታችንስ አልመጣም?
እህት፡- ይመጣል፡፡ እያጠናችሁ ጠበቁኝ ብሏል፡፡

## መልመጃ 2

1. የቤተሰብ አባላት ማን ማን እንደሆኑ ግለጹ::
2. የቤተሰብ አባላት በቤት ውስጥ ያላቸውን ሚና ግለጹ::
3. ከቤተሰብ አባላት መካከል መሆን የምትፈልጉት እንደማን እንደሆነ አስረዱ::
4. ከቤተሰብ አባላት መካከል አንዱን መርጣችሁ ቤት ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚያደርገውን ድርጊት ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ አስረዱ::
5. ከቤተሰብ አባላት መካከል አንዱን መርጣችሁ ቤት ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚያደርገውን አስገራሚ ወይም አስቂኝ ወይም ደስ የሚል ድርጊት በደንብ አተኩራቹ በማዬት ያያችሁት ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በተግባር አሳዩ::

## መልመጃ 3

1. ቀጥሎ የምታዩት የቤተሰብ ምስሎች ምን እንደሚያሳዩ ተናገሩ



መልስ. ---------------





መልስ. ------------------- መልስ. -------------------



መልስ. ----------------------

## መልመጃ 4

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ቤተሰብ ምንድ ነው ?
2. የቤተሰብ ሚና መቅዳት ማለት ምን ማለት ነው ?

## 2.4. መስመር መሞነጫጨርን መለማመድ፣ መስመር መሳልና መቀባት::

ከዚህ ትምህርት በኂላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት:-

- መስመርን ትለማመዳላችሁ
- መስመሮችን ትስላላችሁ
- መስመሮችን ትሞነጫጭራላችሁ
- መስመሮችን በአንድ ላይ በመቀመር ስዕል መሳል ትችላላችሁ


### መስመር ምንድ ነው?

መስመር ከዕይታ ጥበብ ውስጥ መሰረታዊ ከምንላቸው ግብአቶች መካከል አንዱ ነው:: ማንኛውም ሰው ስዕልን ለመሳል ከመጀመሩ በፊት መስመሮችን ማወቅና መለየት አለበት::

መስመር ስንል ማስመሪያዎችን በመጠቀም ወደጎን እና ወደላይ እያደረግን የምናሰምረው ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው ናቸው:: የተለያየ መጠን እና ቅርጽ ያላቸው የተለያዩ አይነት መስመሮች አሉ:: እነዚህም የመስመር አይነቶች ለምንሰላቸው ስዕሎች በተለያየ መልኩ ይገባሉ

## መልመጃ አንድ

**የመስመር አይነቶችን መለማመድ ተማሪዎች፡- እነዚህ ከስር የተቀመጡትን የመስመር አይነቶች በደንብ አስተውላችሁ ማየት እና ለይታችሁ ማወቅ አለባችሁ. መስመሮቹ ከነጥብ ጀምረው ነጠብጣብ፣ቋሚ፣ዝርግ፣አግድም፣ጠመዝማዛ፣ታጣፊ ወዘተ ናቸው፡ ፡**





**ከላይ ምስሉ ላይ ያየናቸው የመስመር አይነቶች እነዚህ ብቻ አለመሆናቸው መታወቅ አለበት፡፡ሌሎችም በርካታ የመስመር አይነቶችም አሉ፡፡**

## መልመጃ ሁለት


መስመሮችን በመጠቀም ከስር የሚታዩትን አይነት የተለያዩ ምስሎችን መሞከር ያስፈልጋል፡፡




በታጣፊ፤ጠመዝማዛ፤ክብ፣መስመሮች የተሳለ ምስል



ስላሽ መስመርን በመጠቀም የተሳለ ምስል



በቋሚ መስመር የተሳለ ምስል



ነጠብጣብ መስመርን በመጠቀም የተሳለ ምስል

## መልመጃ 3

መስመሮቹን ማስመሪያ ሳትጠቀሙ ስሩ፡፡

## መልመጃ 4

መስመሮቹን በማስመሪያ ለመስራት ሞክሩ፡፡




## መልመጃ 5

ምሳሌዎችን በመመልከት የአግድም፣ ጠመዝማዛ የታጣፊ ፣የስላሽ እና የመሳሰሉት መስመሮችን በመጠቀም ስዕል ሥሩ


## ምሳሌ

## ምስል









## መልመጃ 6

### አዛምድ

የሚከተሉትን መስመሮች ከትክክለኛ ስያሜአቸው ጋር አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1 .................. | ሀ. ታጣፊ |
| 2 ______ | ለ. ዚግዛግ |
| 3.  | ሐ. አግድም |
| 4  | መ. ስላሽ |
| 5  | ሠ. ነጠብጣብ |

## ማጠቃለያ

በዚህ ርዕስ የቤተሰብ መዝሙሮችን በመዘመር ስለ ቤተሰብ ፍቅር እና እንክብካቤ የቤተሰቦቻችንን አባላት አውቀናል፡፡ ቤተሰቦቻችንን፣አስተማሪዎቻችንን፣ጓደኞቻችንን ማክበር እንዳለብን ተመልክተናል ውዝዋዜም እንደዚሁ ሰዎች በየዕለቱ የምናደርገው በሰውነት እንቅስቃሴ በመታገዝ የሚከወን ሙዚቃዊ ጥበብ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

ውዝዋዜ የእርምጃዎቻችንን ቅደም ተከተል በመከተል ወደ ሙዚቃዊ ስልተ ምት የመቀየር ጥበብ መሆኑን በተግባር ተመልክተናል፡፡

በሌላ መልኩ የቤተሰቦቻችንን ሚና እንዴት መቅዳት እንዳለብን አይተናል። ከዚሁም በኋላ በሚኖረን እንቅስቃሴ ከቤተሰቦቻችን ጋር ያለን ግንኙነት ጠንካራ መሆን ይኖርበታል።

ከትምህርት በኋላ የሚኖረን የእረፍት ጊዜ የቤተሰቦቻችንን ድርጊቶች ብቻ ሳይሆን የአጎትን፣የአክስትን፣የጎረቤትን ድርጊቶች በማየት መለማመድ እንዳለብን ተረድተናል።

በዕይታ ጥበባት ትምህርት የተለያዩ የመስመርና የምስል ልምምዶችን አይተናል። ልምምዶችን በዚህ ክፍለ ትምህርት ብቻ ይጠናቀቃል ማለት አይደለም። ይልቁን በእረፍት ሰዓታችንም ልምምዶችን ማድረግ ይኖርብናል። ልምምዳችንን መዘናኛም፣መማሪያም በማድረግ ተሰጥዖቻችንን ማሳደግ እንችላለን።

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ምዘና

1፣ አንድ የቤተሰብ መዝሙር ለየብቻችሁ ሆናችሁ ዘምሩ

2፣ የምታውቁትን ዘፈን እየዘፈናችሁ መወዛወዝን አሳዩ

3፣ ድምጻችሁን እንደ አባት ወይም እንደ እናት አድርጋችሁ

ደስ ያላችሁን ነገር አውሩ

4፣ አግድም መስመር ሰርታችሁ አሳዩ

# ምዕራፍ ሦስት

## ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች

### መግቢያ

### 3. ባህል

ባህል ስንል ሰፊና ጥልቅ ሃሳብ ያለው ቃል ነው፡፡ ባህልን ብዙ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጸውታል፡፡

ለምሳሌ፡- የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1993 ዓመተ ምህረት ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ባህል ማለት የአንድ ማህበረሰብ (ህብረተሰብ) የአኗኗር ዘዴ፤ወግ፤እውቀት፤ስነ ጥበብ፤ እምነትን የያዘ(ያካተተ) የታሪክና የማንነትመገለጫ ጥበብ ነው፡ ሃገራችን ኢትዮጵያም የብዙ ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶች ባለቤት ናት፡

የዚህ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች ስለሃገራችሁ ባህል አኗኗር፤እምነት፤ስነ ጥበብ፤ታሪክን፤ማንነትን እናሃገር በቀል ጥበብን እንድታውቁ ማድረግ ነው፡፡

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ።

- መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ።
- በአከባቢያችሁ የሚገኙት ጥበባት ትረዳላችሁ።
- የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ።

## 3.1. በአካባቢውና በማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ መዝሙራት

ከዚህ ንዑስ ርዕሱ በኋላ የሚጠበቅ ዝርዝር የመማር ውጤት ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ፡-

- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ታውቃላችሁ።
- ሀገር በቀል እውቀቶችን፤የዕደ ጥበብ፤ሽመና፤ሸክላ ስራ ፤ግብርና ወዘተ…ታውቃላችሁ።
- ለቋንቋ እድገት እና ለትምህርት ዝግጁነታችሁ ይረዳችኋል።
- የሃገራችሁን ሰንደቅ ዓላማ ቀለማትን ታውቃላችሁ።
- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ።

በአካባቢውና በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ መዝሙራት ማለት በየዕለቱ ለዓይናችን፤ለጆሯችን አዲስ ያልሆኑ የምናውቃቸው መዝሙሮች ናቸው። በቤታችን ፤በአካባቢያችን፣በትምህርት ቤታችን በምስል ተቀርፀው በቴሌቪዥን የሚቀርቡ አዘውትረን የምንመለከታቸው፤የምንዘምራቸው፤ የምናዳምጣቸው፤በሙዚቃዊ ጥበብ ታጅበው ጥበባዊ በሆነ መንገድ ተውበው የሚቀርቡ የክወናና የእይታ ጥበባት ናቸው።

- በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች እንዲሁም ባህላዊ ክዋኔዎች ታላላቆቻችሁን ጠይቃችሁ ለመምህራችሁ ግለፁ።

መዝሙር 1. ከደጋጎች ምድር

ከደጋጎች ምድር......ደጋግ ሃሳብ ያለኝ

ኢትዮጵያ ሃገሬን.......የማስጠራ እኔ ነኝ

እኔ ነኝ.............እኔ ነኝ


ሃገር ተረካቢ........ለደጋግ ልቦች

ሰለም ጤና ይሁን........ለሃገሬ ልጆች

ሰላም ጤና ይሁን.........ለኢትዮጵያ ልጆች


ኢትዮጵያ ሃገሬ
ከደጋጎች ምድር
ተስፋ @የኢትዮጵያ ልጆች ቲቪ





መዝሙር 2. እኛም አለን ሙዚቃ

እኛም አለን ሙዚቃ  ስሜት የሚያነቃ

እኛም አለን ጨዋታ....ለፍቅር  ለደስታ

ክራራችን....መሰንቋችን

በገናችን......ዋሽንታችን

ከበሮችን......እምቢልታችን

ጡሩንባችን.....ጭፈራችን





መዝሙር 3.ኢትዮጵያ ሀገሬ



ኢትዮጵያ...ሀገራችን

ኢትዮጵያ....እናታችን (2 ጊዜ)

በጣም ያኮራኛል ኢትዮጵያዊነቴ
የሃገሬ ፍቅር ጠልቆ በስሜቴ
አንች የነፃነት ጎህ የታሪክ አውድማ
በአለም ተሰራጭቶ ዝናሽ የተሰማ
----አዝማች---

አየርሽ ተስማሚ ሕይወትን የሚያድስ
ነው
ፏፏቴሽ የጠራ የማይደፈርስ ነው
በአየርሽ ተንሳፈው ወፎች ሲዘምሩ
አራዊት እንስሳት በጫካሽ ሲበሩ

ኢትዮጵያ....እናታችን (2 ጊዜ)

ኢትዮጵያ....እናታችን

## መዝሙር 4.ሃገር በቀል ጥበብ

የሃገሬ ሸማኔ በ ጥበብ የሰራው
እማመ ጥጥ ፈትላ አባባ ጋቢ አለው
ሸማኔው ልጅ አለው ሸማኔው ልጅ አለው

አርሶ የሚያበላው ልጁ ገበሬ ነው


ሚስቱ ሸክላ ሰሪ የእጅ ጥበብ አላት

ሸክላ ድስት ጀበና የምትሰራበት
የሃገሬ ልጆች ሰላም እንዴት ናችሁ


ሸማኔ


ገበሬ


ሸክላ ሰራ



መዝሙር 5.  ሰንደቅ አለኝ

ሰንደቅ አለኝ

አረንጓዴ አረንጓዴ ቢ ጫ ቀይ

የተዋበ የነፃነት ሰንደቅ አለኝ፡፡







መዝሙር 6 .ቼ ፈረሴ

ቼ ቼ ቼ ፈረሴ ቼ ቼ ቼ ፈረሴ
ቼ ቼ ቼ ፈረሴ ቼ ቼ ቼ ፈረሴ

ነጭ ፈረስ ላይ.....ተቀምጬለሁ
ቼቼቼ እያልኩ.....እጋልባለሁ
ጥቁርፈረስ ላይ ተቀምጬለሁ
ቼቼቼ እያልኩ.....እጋልባለሁ

----አዝማች----

ቀይ ፈረስ ላይ.....ተቀምጬለሁ
ቼ ቼ ቼ እያልኩ.....እጋልባለሁ
ቡኒ ፈረስ ላይ ተቀምጬለሁ
ቼ ቼ ቼ እያልኩ.....እጋልባለሁ

----አዝማች----




## መልመጃ 1

1. መዝሙሩ ላይ ከተገለፁት ውስጥ የሀገር በቀል እውቀት የሆነው የትኛው ነው፡፡

   ሀ. የሽመና ለ. የሸክላ ስራ

   ሐ. ሁሉም መልስ ነው

2. የኢትዮጲያ ሰንደቅ አላማ ቀለም ስንት ነው፡፡

   ሀ. 3 ለ.4 ሐ. 2

3. የሀገራችን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ የሆነው የትኛው ነው፡፡

   ሀ. መስንቆ ለ. ክራር

   ሐ. ጊታር መ. ሀ እና ለ



ከዚህ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

በዚህ ርዕስ በኋላ ተማሪዎች የሚከተሉትን ትችላላችሁ::

- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ውዝዋዜዎች ትለያላችሁ::
- መዝሙር እየዘመራችሁ ውዝዋዜዎችን ትወዛወዛላችሁ::
- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ጥበባት ትረዳላችሁ::
- የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ::

## 3.2 በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ውዝዋዜዎች

**የውዝዋዜ ጥበብ የሃገርን ታሪክ እና ባህልን ጥበባዊ በሆነ መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ የምናስተላልፍበት የእንቅስቃሴ ጥበብ ነው:: የተሻለ ስሜት እንዲሰማን ያደርጋል:: ውዝዋዜ በግል ወይም በቡድን ሆነን የምንሰራው የክወናና የእይታ ጥበብ ነው::**



መዝሙር 1.ባህሌን አከብራለሁ

ሃገሬን እኔ እወዳታለሁ

ባህሌን በጣም አከብራለሁ

እስክስ እስክስ እላለሁ



ወላይተኛ.....እጨፍራለሁ
ኦሮምኛ.... እጨፍራለሁ
አማርኛ..... እጨፍራለሁ

በትግረኛ...እጨፍራለሁ
ጉራግኛ.....እጨፍራለሁ





መልመጃ 2 ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የሆነውን ምረጡ

1. መዝሙሩ ውስጥ ካየናቸው የባህላዊ ውዝዋዜዎች ውስጥ ቢያንስ ሶስቱን ጥቀሱ፡፡

   1.-------------2. --------------3.-----------

   ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የሆነውን ምረጡ

2. የውዝዋዜ ስሜታችንን ምን ያደርግልናል

   ሀ.ያነቃቃናል ለ.ያስከፋናል ሐ.መልሱ የለም

3. የውዝዋዜ የሀገርን ባህል፣ታሪክ ያስተምራል

   ሀ. እውነት ለ. ሐሰት

## መልመጃ 3

**የግል ፅብረቃ (ቃል ጥያቄ)**

1.ስለ ቼ ፈረሴ የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ።

2. ከሃገራችን ባህላዊ ውዝዋዜዎች ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ።

## 3.3 ተረቶች፣ትረካዎች፣እንቆቅልሽ ጨዋታዎች

### ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ከዚህ ርዕስ መጠናቀቅ በኋላ የሚከተለውን ትችላላችሁ

- ጨዋታዎችን ዘና ብሎ መጫወት ትችላላችሁ
- ተረቶችን ማውራት ትችላላችሁ
- እንቆቅልሾችን መጠያየቅ ትችላላችሁ

ተማሪዎች፡- ከጓደኞቻችሁ ጋር እንቆቅልሽ ተጠያይቃችሁ፤ተረት ተረት አውርታችሁ፤የተለያዩ ጨዋታዎችን ተጫውታችሁ ታውቃላችሁ፣ መልሱን ለመምህራችሁ ተናገሩ

## ተረት ተረት

ተረት ተረት የሚባለው ከድሮ ጀምሮ የነበረ እና ዛሬም ድረስ ልጆች ተሰባስበው እርስ በርስ የሚያወሩት ወይም ከታላላቆቻቸው የሚሰሙት መዝናኛ ነው፡፡

### መልመጃ አንድ

1. ከዚህ በፊት የሰማችሁትን ተረት ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ
2. ቤተሰቦቻችሁ ተረት እንዲነግሯችሁ አድርጉና የሰማችሁትን ተረት ክፍል ውስጥ አውሩት
3. መምህር ከነገሯችሁ ተረት ውስጥ ምን ትምህርት እንዳገኛችሁ አስረዱ

### መልመጃ ሁለት

### እንቆቅልሽ

እንቆቅልሽ ታውቃላችሁ?

እንቆቅልሽ ማለት የጥያቄና መልስ ጨዋታ ሲሆን በጣም የሚያዝናና ከመሆኑም በላይ ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት በምታደርጉት ጥረት የማሰብ ችሎታችሁን ያዳብርላችኋል፡፡

❖ እነዚህን እንቆቅልሾች ከቤተሰቦቻችሁ ጠይቁና መልሶቻችሁን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

## እንቆቅልህ እንቆቅልሽ

1. ዞሮ ዞሮ መግቢያው ጭራሮ
2. ጥቁር አዞ ተጠማዞ
3. ዞራ ዞራ ጥፌ ቀማሽ

እናንተም የምታውቁትን የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች ጠይቁ

## መልመጃ ሶስት

## ልዩ ልዩ ጨዋታዎች

ከጓደኞቻችሁ ወይም ከዕድሜ እኩዮቻችሁ ጋር ሰፈራችሁ ውስጥ፣ ትምህርት ቤታችሁ ውስጥ፣ የምትጫወቷቸው የጨዋታ አይነቶች ናቸው።እነኚህ ጨዋታዎች የመዝናናት ፍላጎታችሁን ከማሟላታቸውም በላይ ጨዋታዎቹ በራሳቸው ጥበባዊ ይዘት ያላቸው በመሆናቸው በአስተዳደጋችሁ፣ ላይ መልካም የሆነ ውጤት ይኖራቸዋል።

የልጆች ጨዋታዎች እጅግ በርካታ ናቸው። ነገር ግን ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉትን የተወሰኑ ጨዋታዎችን እንጥቀስ

### 1ኛ. አኩኩሉ ወይም ድብብቆሽ፣

ይህ ጨዋታ ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆች በጋራ የሚጫወቱት የጨዋታ አይነት ሲሆን አጨዋወቱ ደግሞ፣ ከልጆቹ መሃል አንደኛው ተመርጦ ቆጣሪ ይሆንና ፊቱን በእጁ ሸፍኖ ከ አንድ እስከ አስር ወይም እስከ መቶ ቀስ እያለ በሚቆጥርበት ጊዜ ሌሎቹ ጓደኞቹይደበቁበታል።

ወይም ደግሞ ቆጣሪው ልጅ ፊቱን ሸፍኖ ድምጹን ከፍ አድርጎ አኩኩሉ ሲላቸው ጓደኞቹ መደበቂያ ቦታ እስከሚያገኙ ድረስ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አልነጋም እያሉ ይመልሱለታል፡፡



## 2ኛ ገመድ ዝላይ

የገመድ ዝላይ ጨዋታ ሁለት አይነት መልክ አለው፡፡ ይኸውም፣ አንደኛው ለብቻ ሆነው የሚጫወቱት እና ሁለተኛው ሁለት ሰዎች ገመዱን እያሽከረከሩ አንድ ሰው መሀል ላይ ይዘላል





ሌላው ደግሞ ሶስት ልጆች ሆነው የሚጫወቱት ነው፡፡

## 3ኛ. መሐረቤን ያያችሁ

ይህ የጨዋታ አይነት ከአስር የማያንሱ ልጆች ሴቶችም ወንዶችም ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ተቀላቅለው ክብ ሰርተው መሬት ላይ ይቀመጡና አጫዋች የሆነው ልጅ ክብ ሰርተው ከተቀመጡት ልጆች ጀርባ ሆኖ መሐረቡን በእጁ ይዞ ወይም ልብሱ ውስጥ ደብቆ ክብ ሰርተው በተቀመጡት ልጆች ዙሪያ እየተሽከረከረ በዜማ መሐረቤን ያያችሁ ሲል የተቀመጡት ልጆችም አላየንም እባካችሁ እያሉ በዜማ ይመልሱለታል፡፡

መሐረቤን ያያችሁ

መሐረቤን ያያችሁ
....አላየንም እባካችሁ
መሐረቤን ያያችሁ ....አላየንም
እባካችሁ {2x}

ይቺ ምንድናት የውርዬ ኳስ ናት

ይቺ ምንድናት የውርዬ ኳስ ናት



## መልመጃ አራት

1. የትኛውን ጨዋታ የበለጠ ወደዳችሁት
2. ሌላ እናንተ ምን አይነት ጨዋታ ታውቃላችሁ

### 3.4. በአካባቢ ያሉ ቀለማት

ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

- ቀለማት የት እንደሚገኙ ታውቃላችሁ
- ቀለማት በባህል ከህብረተሰቡ ውስጥ የሚወጣቸው ትርጓሜ ትረዳላችሁ
- የሀገራችን ሠንደቅ አላማ  ቀለማትና ትርጓሜ ትረዳላችሁ
- በሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮ ላይ የሚገኙ ቀለማት ትለያላችሁ

**መግቢያ**

ተማሪዎች በአካባቢው ያሉ ቀለማት ስንል የአንድ ህዝብ ባህል ውስጥ የሚገኙ ሰው ሰራሽ ነገሮች ላይ እና በተፈጥሮ የሚገኙ ቀለማት ማለታችን ነው፡፡

ተፈጥሮ በራሱዋ የምትሰጠን ልዩ ልዩ ቀለማት በአካባቢያች አሉ፡፡ በአዲስ ዓመት ዘመን መለወጫ ሀገራችን በቢጫ ቀለም ባላቸው አደይ አበቦች ታሸበርቃላች፡፡

በአረንጓዴ እና በሰማያዊ መልካአምድር የተዋበ ተፈጥሮ ቆጥረንና አይተን የማንጨርሳቸው የቀለማት አይነቶችም አሉ በአዕዋፋት፣በእንስሳት፣ በሰዎች ልጆች ሠይቀር ቀለማት የተለያዩ ነው፡፡

በምንመገበው ምግብ፣ ፍራፍሬ እናም በምንለብሰው ልብስ በቤታችን የተቀባው የግድግዳ ቀለም በምንገለገልባቸው ቁሳቁሶች ሳይቀር ቀለማት የተለያዩ ሰዎች በባህላቸው አስበው ይጠቀሙባቸዋል፡፡

ምሳሌ









በሰው ሰራሽ ነገሮች ላይ የሚገኙ ቀለማት





ሰንደቅ አላማችን ላይ የሚሰጠው ትርጓሜ

አረንጓዴ: እድገት እና ልምላሜ

ቢጫ: ተስፋና ፍትህ

ቀይ: መስዋትነት

በመሀሉ የሚገኘው ኮከብ እና መስመሮች «የኢትዮጵያ» ህዝቦች አንድነትና የወደፊት ብሩህ ራዕይ ያመለክታል፡፡

በአካባቢያችን ባህል ቀለማት የሚሰጣቸው ትርጓሜ በጥቂቱ

- ጥቁር: በሀገራችን በሀዘን ወቅት ጥቁር ልብስ መልበስ የተለመደ ነው፡፡
- ነጭ:- በደስታና፣ በሰርግ በመሳሰሉት ነጭ ልብሶች መልበስ የተለመደ ነው፡፡
- በበአላት ወቅት የተለያዩ ቀለማትን ተጠቅሞ ቤትንና አካባቢን ማሸብረቅ የተለመደ ነው፡፡

## ምስል





### የትራፊክ ህግ ቀለማት

ቀይ:ቁም

ቢጫ : ተጠንቀቅ እና ተዘጋጅ

አረንጓዴ: ሂድ

### መልመጃ 1


ምስሎቹን ከቀለማቶቻቸው ጋር አዛምዱ

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1.አረንጓዴ ቀለም | ሀ.የትራፊክ መብራት |
| 2.ቢጫ | ለ.የኢትዮጰያ ሠንደቅ አላማ |
| 3.ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ | ሐ.ዛፎች፣ቅጠሎች፣ሳር |
| 4.ሰማያዊ | መ.ሰማይ |
| 5.አረንጓዴ ፣ቢጫ፣ ቀይ | ሠ.አደይ አበባ |

## መልመጃ 2

1.፤ የትራፊክ መብራት ስዕሉን በመስራት የቀለማቱን ትርጓሜ ጻፉ

ምስል




## መልመጃ 3

2.፤ ሠንደቅ አላማችንን በመሳል የቀለማቱን ትርጓሜ ጻፉ

| ስዕል | ትርጓሜ |
| --- | --- |
| | |
| | |
| | |

በአካባቢያችሁ ያሉ መዝሙራትን፣ ድምፆችን፣ ምስሎችንእና ቀለማትን በማጤን እና በመረዳት አውቃቹሃል። የዕለት ተዕለት የአኗኗራችሁን ዘዴ፣ወግ፣እውቀት፣ስነ ጥበብ፣ እምነትን የያዘ(ያካተተ) ታሪካዊ እና ሃገር በቀል እውቀትን፣ ማንነታችሁን መገለጽ የምትችሉበት ጥበብ ነው።

በዚህ ርዕስ የተማርነው በአካባቢያችን ያሉ መዝሙራትን፣ድምፆችን፣ የተለያዩ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ማጤን እና አውቀን መረዳትነው። የዕለት ተዕለት የአኗኗራችንን ዘዴ፣ወግ፣እውቀት፣ስነ ጥበብ፣እምነትን የያዘ(ያካተተ) ታሪካዊ እናሃገር በቀል እውቀትን አውቀናል።

ባህል ለአንድ ማህበረሰብ የማንነቱ መገለጫ መሆኑን እንድንረዳና እና እንድናውቅ ያደርገናል። ከዚህ በኋላም በሚኖረን እድገት ማንኛውም እንቅስቃሴያችን ውስጥ ባህላችንን የምንረዳ የምናከብር የምንወድ የምናደንቅ እንድንሆን የሚያስተምር ሃሳብ የያዘ የክወና ጥበብ አካልነው።

ተረቶች እንቆቅልሾች እንዲሁም ልዩ ልዩ ጨዋታዎች የልጆችን መንፈስ የሚያድሱ ከመሆናቸውም በላይ ማህበራዊ ህይወታቸውን የተቃና ያደርጋሉ።

መዝናናት ሲኖር አእምሮ በአግባቡ ማሰብ ያለበትን ማሰብ ይችላል። ተማሪዎች ለትምህርታቸው የሚኖራቸው ፍቅር ዘላቂ እና ጠንካራ ይሆናል ስለዚህ በዚህ ርዕስ ስር ከታዩት ጨዋታዎች ባሻገር ሌሎችንም ባግባቡ ቢጫወቱ ጥሩ ነው።

# ምዕራፍ አራት

## ሥነ-ውበታዊ እሴት

### መግቢያ

ሥነ-ውበታዊ እሴቶችን ዋጋ መስጠት ባህላዊ ሃብቶቻችንን መልካም የሆኑ ልምዶችን ማድነቅ ለአንድ ማህበረሰብ ተገቢ ተግባር ነው:: ሰዎች የራሳቸውን እና የሌሎችን ሥነ-ውበታዊ እሴቶችን እና ባህላዊ እሴቶችን የእምነት እና የአኗኗር ስርዓቶችን በማድነቅ ክብር መስጠት ያስፈልጋል:: ባህሎቻችንን በትምህርት ቤት በሰፈር በተለያዩ አጋጣሚዎች ባህላቸውን የሚያደንቁበትን የሚያከብሩበትን የባህል ሳምንቶችን በማዘጋጀት ሁኔታዎች በማመቻቸት እንዲያውቁና እንዲረዱ ማድረግ ነው::ስለራሳችሁ ባህል ያላችሁን ግንዛቤ በመጨመር የሀገራችሁን ሥነ-ውበታዊ እሴቶችን እንድታውቁ እንድታከብሩ ማድረግ ነው::

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ፡፡

- መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፡፡
- በአከባቢያችሁ የሚገኙት ጥበባት ትረዳላችሁ፡፡
- የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ድምፆችን፣ ሥዕሎችንና ቀለሞችን ይለያሉ፡፡

## 4.ባህላዊ ልምዶችን ማድነቅ

ከዚህ ንዑስ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

በዚህ ንዑስ ርዕስ በኋላ ተማሪዎች የሚከተሉትን ትችላላችሁ፡፡

- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ድምፆችን፤ባህሎችን ትለያላችሁ፡፡
- መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፤ጨዋታዎችን ትጫዎታላችሁ፡፡
- በሃገራችሁ፤በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ጥበባት ትረዳላችሁ፡፡
- የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ፡፡
- ለቋንቋ እድገት እና ለትምህርት ዝግጁነታችሁ ይረዳችኋል፡፡
- በአከባቢያችሁ የሚገኙትን የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ፤ ትረዳላችሁ፡፡
- ታሪካችሁንና ባህላዊ ልምዶችን ታደንቃላችሁ፡፡

- ባህላዊ ልምዶችን ማድነቅ ማለት ምን ማለት ነው?

ባህላዊ ልምዶችን ማድነቅ ማለት ህዝቦች የራሳቸውን እና የሌሎችን ባህል የባህል እሴቶችን እምነት እና የአኗኗር ስርዓቶችን ማድነቅ ክብር መስጠት ነው። ስለራሳችን ባህል ያለንን ግንዛቤ በመጨመር ባህልን ማወቅ እና ማድነቅ ማለት ነው። የባህል እሴቶችን ታሪክን፣አኗኗር ዘዴን፣እምነታችንን፣ስነ ጥበባዊ እሴቶችን ለሌሎች ሰዎች ማሳወቅ፣ መናገር፣ መማር፣ ማድነቅ ማለት ነው።

- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ባህላዊ ልምዶች ታላላቆቻቸሁን በመጠየቅ ለመምህራችሁ ግለፁ።
- በምስልና በድምጽ የተዘጋጀውን መዝሙር በመመልከት በታላላቆቻችሁ በመታገዝ አዳምጣችሁ የመዝሙሩን አጠቃላይ መልዕክት ለመምህራችሁ አስረዱ።
- የመዝሙሩን መልዕክት ምን ማለት እንደሆነ መምህራችሁ የሚጠይቋችሁን በመስማት መልሱ።

## 4.1 የቤተሰብ መዝሙር

ከዚህ ንዑስ ርዕሱ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

በዚህ ንዑስ ርዕሱ በኋላ የሚከተለትንት ችላላችሁ።

- መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ ባህላችሁን ታደንቃላችሁ።
- በሃገራችሁ፤ በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ጥበባት ትረዳላችሁ።
- ታሪካችሁን እና ባህላዊ ልምዶችን ታደንቃላችሁ።

መዝሙር 1.

ያምራል ሃገሬ

ያምራል ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬ...አረ ያምራል ሃገሬ(2.ጊዜ)

ባህል አለኝ እኔም በጣም የሚያኮራ
ያምራል ሃገሬ አረ ያምራል
ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬ ጥንት በአባቶቼ ጥበብ
የተሰራያምራል ሃገሬ አረ ያምራል

ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬያምራል ሃገሬ አረ ያምራል
ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬ (2. ጊዜ)

ሌላ ሃገር የለኝም ባንች ነው ማማሬ...ያምራል ሃገሬ
ያምራል

ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬ አንች ስትኖሪ ነው እኔ መከብሬ...
ያምራል ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬ

ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬ አረንጓዴ ቢጫ ቀዩ ሰንደቅሽ....
ያምራል ሃገሬ አረ ያምራል

ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬ
የስልጣኔ በር ሃገሬ አንች ነሽ...ያምራል ሃገሬ አረ ያምራል

ሃገሬ አረ ያምራል ሃገሬ



መልመጃ.1

1. ባህል አለኝ እኔ-------------

ጥንት በአባቶቼ------------የተሰራ ?

2. ---------------------ሰንደቅሽ
የስልጣኔ በር ሃገሬ አንች ነሽ



መዝሙር 2.

አባይ የኔ ነው

- በምስልና በድምጽ የተዘጋጀውን መዝሙር በመመልከት በቤተሰቦቻችሁ በመታገዝ አዳምጣችሁ የመዝሙሩን አጠቃላይ መልዕክት ለመምህራችሁ አስረዱ::
- ተማሪዎች የመዝሙሩን መልዕክት ምን ማለት እንደሆነ አስረዱ

መምህራችሁ የሚጠይቋችሁን በመስማት መልሱ፡፡

አባይ የኔ ነው ዓ....ባይ...ዓባይ የኔ ነው....
የኔ ነው የኔዓባይ ቅኔ ነው...ቅኔ ነው ቅኔ
የእናት ኢትዮጵያ ያብራኳ ክፋይ
የሚፍለቀለቅ አምባዎቿ ላይዓ.....ባይ

ዓ....ባይ...ዓባይ የኔ ነው ህያው ታሪኬ
የተኳለበት ኩራቴ መልኬ የኔ ወዘና
የናት ያባቴ ታሪኬ ውርሴ ዓባይ ህይወቴ...
..ዓ.....ባይ በፍቅር ገመድ...ያስተሳሰረን
ዓባይ ማሰሪያው ያንድነታችን
ዓባይ የኔ ነው የእናት ሃገሬ የነገ
ብርሃን ኩራቴ ክብሬ ዓ.....ባይ

ዓ.....ባይ...የ...ኔ....ነው፡፡



## መልመጃ.2

1. ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. አባይ.........ነው ።

ሀ. የኔ ለ. የእነሱ ሐ. መልሱ የለም

2. ዓባይ የኔ ነው ህያው -----------

የተኳለበት------------መልኬ

ሀ. የናት፣ያባቴ ለ. ታሪኬ፤ኩራቴ ሐ. የኔ፤ቅኔ

## መዝሙር 3. ኑ መምህሬ

- በምስልና በድምጽ የተዘጋጀውን መዝሙር በመመልከት በቤተሰቦቻችሁ በመታገዝ አዳምጣችሁ የመዝሙሩን አጠቃላይ መልዕክት ለመምህራችሁ አስረዱ።



## ኑ መምህሬ

ኑ መምህሬ.....ኑ መምህሬ....ኑ መምህሬ ባንተኮ
ነው መመስገኔ መከበሬ ምስጋና ይድረስህ ውዱ
መምህሬ  ምስጋና ይድረስሽ ምርጧ መምህሬ
ያልተዘመረለት የቀለም አባቴለኔ ማክብሬ ነው
ኩራቴ ድምቀቴኑ መምህሬ.....ኑ መምህሬ....ኑ
መምህሬ ባንተኮ ነው መመስገኔ መከበሬ
ለኔማ ክብሬ ነው ኩራቴ ድምቀቴ

ኑ መምህሬ






## መልመጃ 3.

ከግጥሙ የጎደለውን ዓረፍተ ነገር በክፍት ቦታው ላይ በማስቀመጥ መልሱ፡፡

1. ምስጋና ይድረስህ ----------------
   ምስጋና ይድረስሽ-----------መምህሬ
2. ያልተዘመረለት የቀለም-----------
   ለኔማ ክብሬ ነው ኩራቴ ድምቀቴ

## መዝሙር 4. እምዬ ኢትዮጵያ ክብርና ኩራቴ

- በምስልና በድምጽ የተዘጋጀውን መዝሙር በመመልከት በቤተሰቦቻችሁ በመታገዝ አዳምጣችሁ የመዝሙሩን አጠቃላይ መልዕክት ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡
- የመዝሙሩን መልዕክት መምህራችሁ የሚጠይቋችሁን በመስማት መልሱ፡፡



እምዬ ኢትዮጵያ ኩራቴ ነሽ
ክብሬ እምዬ ኢትዮጵያ ኩራቴ ነሽ
ክብሬ እድለኛነት ነው ባንቺ መጠራቴ
ከጥንት መሰረትሽ በቅኝ ያልተገዛሽ
በታሪክ ባህልሽ በዝተሽ የታደልሽ
የሊቃውንት ምድር ባለብዙ ምስጢር
የሰው ልጅ መገኛ በእምነት መዳኛ
በጥበብ በዜማ እውቅናን ያገኘሽ
በፊደል በቁጥር መለያ የተሰጠሽ
እምዬ ኢትዮጵያ ኩራቴ ነሽ ክብሬ
እድለኛነት ነው ባንች መጠራቴ

## መልመጃ.4

1. ከጥንት መሰረትሽ-----------ያልተገዛሽ

   በታሪክ ባህልሽ ብዝተሽ የታደልሽ

2. ---------------ኩራቴ ነሽ ክብሬ

   እድለኛነት ነው ባንች መጠራቴ

## 4.2 ውዝዋዜ

ከዚህ ትምህርት በኋላ ዝርዝር የመማር ውጤት፡-

- የሃገራችሁን የባህል ውዝዋዜ ታውቃላችሁ፤ታደንቃላችሁ፡፡
- በአከባቢያችሁ የሚገኙትን የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ፡፡
- ዜማን ጠብቃችሁ በቀላል ምቶች መወዛወዝ ትችላላችሁ፡፡

የውዝዋዜ ጥበብ ድንቅ በሆነ የሰውነት እንቅስቃሴ በመታገዝ ታሪካችሁን እና ባህላችሁን ከትውልድ ወደ ትውልድ የምታስተላልፉበት ጥበብ ነው፡፡ ውዝዋዜ በግል ወይም በቡድን ሆነን የምንሰራው የክወናና የእይታ ጥበብ ነው፡፡

- የተለያዩ የሀገራችንን ባህላዊ ውዝዋዜዎች ታላላቆቻችሁን በመጠየቅ ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡
- ምዕራፍ ሁለት ላይ ከተማሯችኂቸው ውዝዋዜዎች ውስጥ የምታውቋቸውን የውዝዋዜ አይነቶች በማስታወስ ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡

መዝሙር 5. ባህሌን አደንቃለሁ


- ተማዎችየመዝሙሩን መልዕክት ምን ማለት እንደሆን መምህራችሁ የሚጠይቋችሁን በመስማት መልሱ፡፡




## ባህሌን አደንቃለሁ

ሃገሬን እኔ እወዳታለሁ
ባህሌን በጣም አከብራለሁ
ታ..ታ..ታ..ታ እላለሁ

አፋርኛ.....እጨፍራለሁ
ሱማልኛ.... እጨፍራለሁ
ሃረርኛ..... እጨፍራለሁ
ጋምቤልኛ...እጨፍራለሁ
ሃመርኛ.....እጨፍራለሁ



## መልመጃ 5.

1. ከሃገራችን ኢትዮጵያ የውዝዋዜ ጥበብ ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ?

1------------2-----------

2. ሃገሬን እኔ እወዳታለሁ ……… በጣም አከብራለሁ

ሀ. ባህሌን ለ. ውዝዋዜን ሐ. ሁሉም መልስ ነው፡፡

## 4.3 ልጆች የባህላዊ ጨዋታ ልማዶችን ማድነቅ

ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት፡፡

- የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን ታውቃላችሁ፡፡
- ተረቶችን ማውራት ትችላላችሁ፡፡
- እንካ ሰላንትያን መጫወት ትችላላችሁ፡፡

### ባህላዊ ጨዋታዎች

በሀገራችን በርካታ ባህላዊ ጨዋታዎች መኖራቸውይታወቃል፡፡ እነዚህ ባህላዊ ጨዋታዎች ከትውልድ ትውልድ እየተላለፉ አሁንም ድረስ ይኖራሉ፡፡ ከነዚህ ባህላዊ ጨዋታዎች መካከል የተወሰኑት

1 የገና ጨዋታ

2 ተረት ተረት

3 እንቆቅልሽ ወዘተ ናቸው

ጨዋታዎች

ሌሎች ባህላዊ ጨዋታዎችን ከታላላቆቻችሁ ጠይቃችሁ መልሱን ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

## 1 የገና ጨዋታ



በዓል ጋር ተያይዞ የሚመጣ ጨዋታ ነው፡፡ገጠር ከከተማ ወጣቶችና ጎልማሶች የሚያዘወትሩት ቢሆንም፣አዛውንቶች መርቀው ከመክፈት ባሻገር አልፎ አልፎ የሚጫወቱ አይጠፉበትም፡፡


## መልመጃ 1

ተማሪዎች ስለገና ጨዋታ ምን ተሰማችሁ

## 2 ተረት ተረት

ስለ ተረት ተረት ባለፈው ክፍለ ጊዜ ተምራችኋል አሁን ደግሞ ይህንን ተረት በተራ በተራ እየተቀበቀበላችሁ አንብቡ

ስግብግቡ ጅብና ብልጧ አህያ



አንድ ጊዜ አንድ ጅብና አህይት መንገድ ላይ ተገናኙ፡፡ “እንደምን ዋልሽ?” አለ ጅብ፡፡ “እግዚአብሔር ይመስገን!” አለች

አህይት፡፡ “ወዴት እየሄድሽ ነው?” አለ ጅብ፡፡ “ውሃ ልጠጣ ወደ ወንዝ እየወረድኩ ነው” አለች፡፡ “እንዴት ያለ ገጠመኝ ነው? እኔም እኮ እንዳንቺው ውሃ ልጠጣ ወደ ወንዝ እየወረድኩ ነው፡፡ በይ አብረን እንሂድ!” አለና ጅቡ ሳቀ፡፡

ምሳ ሰዓት ነበር፡፡ እያወሩ ጎን ለጎን መሄድ ጀመሩ፡፡ ቀኑ በጣም ሞቃታማ ስለነበር ደክሟቸውም ስለነበር ከአንድ ዛፍ ጥላ ስር አረፍ አሉ፡፡ “ለመሆኑ አንቺ የምትኖሪበት ቦታ አንችን የመሳሰሉ ብዙ ቆንጆዎች አሉ?” አላት ጅብ እያጋነነ በማድነቅ፡፡ “እግዚአብሔር ከአይን ይሰውረን እንጂ ብዙ ነን፡፡ ሁሉም ታዲያ ሲበዛ ቆንጆዎች ናቸው፡፡” ጅቡ የፈለገው ዘሎ አህያዋን መዘንጠል ብቻ ነበር፡፡ “በሰፈራችሁ ጨርሶ ውሃ የለም?” ሲል ጠየቃት፡፡ “የለም በክረምት ብዙ ውሃ እናገኛለን፡፡ ምንጮቹም በየቦታው ይፈልቃሉ፡፡ ቀድተን ሁሉ ወደ ቤታችን እንወስዳለን፡፡ አሁን ግን በበጋ ምንጮቻችን ባዶ ናቸው፡፡ ስለዚህ ጥማችንን ለማርካት ወደ ወንዙ እንወርዳለን፡፡ በአንተ ሰፈርስ እንዴት ነው? ምንም ውሃ የለም?” አለችው፡፡ “በፍፁም! እኔ በምኖርበት ቁጥቋጦ ወንዝም ሆነ ምንጭ የለም” አላት፡፡ “ታዲያ ለምን ውሃ ወዳለበት ሠፈር አትሄድም?” “ስለለመድኩት ነው፡ ፡ ከለመዱት እኮ መቃብርም ይሞቃል” አላት ተንከትክቶ እየሳቀ፡ ፡ “እስከዚህ ሞኝ አትሁን፤ እስካለህ ድረስ ሕይወትህን መጠበቅ አለብህ!” አለችው፡፡ “በይ ብዙ አረፍን፤ ጉዟችንን እንቀጥል” አለ ጅቡ ቆሞ እየተወጣጠረ፡፡ “በይ ሂጂ ቅደሚ!” አላት፡፡ “እኛ ሀገር ወንድ ነው ከፊት የሚሄደው፡፡ ምክንያቱም መንገዱን የሚውቀው እሱ ስለሆነ ይመራናል፡፡ ስለዚህ አንተ ቅደም!” አለችው፡፡ “በእኛ ሀገር ደግሞ ተቃራኒው ነው” አላት ከፊት ለፊቷ እየሄደ፡፡ “ሴቶች ይቀድማሉ፤ ወንዶች ይከተላሉ፡፡ በዚህ አይነት በሴቷ ላይ አደጋ ቢደርስ ወንዱ ወዲያው ከአደጋ ሊያድናት ይችላል” በማለት እያስረዳት ከፊት እንድትቀድም ይገፋፋታል፡፡ይሁን እንጂ አህይት በተደጋጋሚ ከኋላ ሆና መሄድ አንደምትፈልግ ትነግረዋለች፡፡

የሆነ ሰዓት ላይ የጅቡ ፀባይ እያስፈራት መጣ፡፡ አድብቶ መጥፎ ነገር ሊፈፅም ነው ስትል አሰበች፡፡ ጅቡ ወሬውን በመቀጠል ከፊት ቀድማ እንድትሄድ ሊያሳምናት ቢሞክርም አህይት ግንለማምለጥ ወሰነች፡፡ ከዚያም ዞረችና ፈረጠጠች፡፡"እባክሽ ነዪና ከፊት ቅደሚ!" አለ ጅቡ ትእግስቱ እያለቀና ከመጎምዠቱ የተነሳ ምራቁን እየዋጠ፡ ፡ ምንም መልስ ሲያጣ ጊዜ ዞር ቢል በሩቁ የአቧራ ደመና ታየው፡፡

ከዜና ማርቆስ እንዳለ

## መልመጃ ሁለት

1ኛ ከተረቱ ምን ተረዳችሁ

2ኛ ስለተረቱ ምን አስተያየት አላችሁ

3ኛ ጅቡን እና አህያይቱን አስመስላችሁ ከውኑ

## 3 እንቆቅልሽ

እንቆቅልሽ ማለት ሰዎች ጥያቄ እየተጠያየቁ አእምሮአቸውን የሚያዳብሩበት ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡

እነዚህን እንቆቅልሾች እየተጠያየቃችሁ አእምሮአችሁን አዳብሩ

- እንቆቅልሽ/ህ ምን አውቅልህ
- የአህያ መቃብር ምንድን ነው?

መልስ፡-

- ግንዱ ወደ ላይ ባላው ወደ ታች?

  መልስ፡-

- ቆፍቋፊት ሞላጭትን ወለደች፣ሞላጭት ቆፍቋፊትን ወለደች?

  መልስ፡-

- ዞራ ዞራ ጥፊ ቀማሽ ?

  መልስ፡-

- አንድ ጊዜ ተዘርቶ ሁለተኛ የማይዘራ፣ታጭዶ ምርት የማይገኝበት ምንድን ነው?

  መልስ፡-

- አንዲት ግንድ በሁለት ትክሻ ትጓደድ ምንድንነው?

  መልስ፡-

## መልመጃ ሦስት

1፣ ከተጠቀሱት የእንቆቅልሽ ጨዋታዎች ሌላ የምታውቁትን እንቆቅልሾች ጠይቁ

2፣ ከእንቆቅልሾቹ ውስጥ ባህላዊ ጉዳይ ላይ ያተኮሩት የትኞቹ ናቸው

## መልመጃ አራት

ቀጣዩን የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ

እንቆቅልሽ/ህ ምንአውቅልሽ/ህ

- ነጩ በሬ አዟሪ፣ቀዩ በሬ በርባሪ፣ምንድን ነው?
- አባ ሲሉት ቆብ የሌለው ምንድን ነው?
- አፉ ዝም ብሎ በእጁ የሚናገር ምንድን ነው?
- ዞሮ ዞሮ እግሩን የማይታጠብ ምንድን ነው?
- የሰጡትን የሚበላ፣ ውሃ ሲያጠጡት የሚሞት ምንድንነው?

### 4.4. ባህላዊ ልምዶችን በምስል ማድነቅ

ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ይህንን ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ

- ባህላዊ ልምዶች ምን እንደሆኑ ትረዳላችሁ
- ባህላዊ ልምዶች በምስል ታደንቃላችሁ
- ባህላዊ ልምዶችን በህብረተሰቡ ውስጥ በማከናወን ለማህበረሰቡ በጎ ያደረጉ በምስል ታውቃላችሁ

## ባህላዊ ልምዶችን በምስል ማድነቅ

ባህላዊ ልምዶች ማለት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው በየእለቱ፣ በየአመቱ፣ ሊከናወኑ የሚችሉና ተቀባይነት ያላቸውና የተወደሱ ምግባራት ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

ቡና አፈላል፣ በአላትን ተሰባስቦ ማክበር፣ እርስ በርስ መረዳዳት፣ በሀዘን ፣በደስታ አብሮ መሆን፣ ባህላዊ ምግቦች ፣ልብሶች፣ የባህል ጭፈራዎች፣ ወዘተ ባህላዊ ልምዶች እንላቸዋለን፡



### መልመጃ አንድ

ምስል ተማሪዎች ከላይ ያለውን ከተረዳችሁ በኃላ ስለ ባህላዊ ልምዶች ያወቃችሁትን በክፍል ውስጥ አብራሩ

- ምስሎቹን በመመልከት የሚገልጹት ሀሳብ ተናገሩ

ተማሪዎች በስዕል ደብተሮቻቸው በእለት እለት ኑሮዎቻቸው ውስጥ የሚያከናወኑ ባህላዊ ድርጊቶችን በስዕል ሳሉ፡፡

ምሳሌ፡ ቡና ማፍላት

## ባህላዊ ልምዶች ከዕይታ ጥበብ ጋር

በዕይታ ጥበብ ባህላዊ ልምዶች በመሳልና መልዕክቶችን በማስቀመጥ፣ የተለያዩ ስጦታዎችን በመለዋወጥ ለጓደኞቻችን ለወላጆቻችን እና ለዘመድ አዝማድ ደስታን መፍጠር ይቻላል፡፡

ምስል 1

በባህላችን ወቅት፣ በደስታ ጊዜ መልካም ምኞትን የሚያስተላልፉ የስጦታ ካርዶችን መለዋወጥ የተለመደ ነው፡፡





ምስል 2

በበዓላት ግዜ ቤትን አካባቢን በዕይታ ጥበባዊ ድርጊቶች ማሸብረቅ ማስዋብ የተለመደ ነው







ምስል 3

ልጆች በበዓላት ግዜ ያላቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የተወደደና የተወሰደ ባህላዊ ልማዶች መሀል በእንቁጣጣሽ ግዜ የተዋቡ ሥዕሎች እየሳሉ ለጎረቤት/ በቤተሰብ ያበረክታሉ




ምስል 3 የእንቁጣጣሽ ስዕል አሰራር

## መልመጃ ሁለት

የእንቁጣጣሽ ስዕል አሰራርን አይታችሁ ተለማመዱ

1. መጀመሪያ ምን መሳል እንደምትፈልጉ ማሰብ
2. በዛ ያለ ወረቀትና/ ካርቦን/ማዘጋጀት
3. ቀለምና ብሩሽ/ ወይንም የእርሳስ ከለር

ያሰብነውን ሀሳብ በእርሳስ ስዕል በካርቦኑ ደግሞ አሰደግፈን ሌሎች ተጨማሪ እንዲሆንልን ማብዛት



- ከዛም ባዘጋጀነው ቀለም መቀባት
- ስማችንን እና ቀን ከስዕሉ ስር መጻፍ
- ሰርተን ስንጨርስ እጃችንን መታጠብ

## ባህላዊ ድርጊቶች የሚሰጡትን ጠቀሜታ በጥቂቱ

1. ደስተኛ ያደርጋል
2. ረዥም እድሜ ይሰጣል
3. ጭንቀት ይቀንሳል
4. ብቸኛ እንዳንሆን ያደርጋል
5. ለመልካምነት ያነሳሳል

ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ያሉ፣ መልካምና በጎ ተግባራትን ስናከናውንና ስናደንቅ በአካባቢያች ደስተኞች እንሆናለን

ተማሪዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ባህላዊ ድርጊቶችን አብሮ መብላትን ያላቸውን ማካፈልን፣ የስራ ባህልን፣ ተባብሮ መስራትን፣ አረጋውያንን መጦርን በይበልጥ የተገበሩ ሰዎች እንዳሉ ታውቃላችሁ?

- በእናንተ አካባቢ በጎ የምትሉት ሰው ማነው?

ከላይ እንደተማራችሁት የተለያዩ ባህላዊ ድርጊቶችን በምስል አይታችኋል። አሁን ደግሞ አረጋዊያንን በመንከባከብ የተራቡ ለማብላት ስራንና ጊዜን በማክበር ያላቸውን በማካፈል በህብረተሰቡ ዘንድ የተወደሱ መልካም ሰዎችን እናስተዋውቃችሁ፡



አበበች ጎበና



ሲ/ር ዘቢደር



ወ/ሮ ዘኒ የኑስ



አርቲስት ስለሺ ደምሴ(ጋሽ አበራ ሞላ)



እጅግ የተከበሩት የአለም ሎሬት
ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ

- የመቆጾኒያ መስራች የሆነው በጎ ሰው ማን ነው

## የማጠቃለያ መልመጃ

### መልመጃ 1

1. የምስሎቹን ትክክለኛ ስያሜዎች አክብቡ



ሀ.ባህላዊ የቡና ስነስርዓት ሐ. ባህላዊ ሙዚቃ

ለ. ሆያ ሆዬ መ. መልስ የለም

2. የምስሎቹን ትክክለኛ ስያሜዎች አክቡባቸው



ሀ. ሆያሆዬ ሐ. እስክስታ

ለ. አበባየሆሽ መ. መልስ የለም

3.የምስሎቹን ትክክለኛ ስያሜዎች አክቡባቸው



ሀ/ አዛውንቶች ማክበር ሐ/ መጨፈር

ለ/ መጣላት መ/ መደነስ


4. ምስሉን በመመልከት የየትኛው በዓል አከባበር መሆኑን ግለጹ



ሀ/ እንቁጣጣሽ ለ/ ገና

ሐ/ ሆሳህና መ/ መልስ የለም

5. ከስር የምትመለከቱት የበጎ ሰው ምስል ማን ይባላል



ሀ/ የመቆዶኒያ መስራች ቢኒያም በለጠ ለ/ አበበች ጎበና

ሐ/ ሰለሞን ቦጋለ መ/መልስ የለም

6. ምስሉን በመመልከት ምን አይነት አሳሳል እንደሆነ ተናገሩ



## ማጠቃለያ

ከላይ መግቢያ ላይ በርካታ ባህላዊ ጨዋታዎች መኖራቸው ተገለጧል ተማሪዎችም በዚህ ክፍለ ትምህርት ከአያችኋቸው ባህላዊ ጨዋታዎች ሌላ ከታላላቆቻችሁ እየጠየቃችሁ መረዳት እንዲሁም መጫወት አለባችሁ፡፡

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ እንደተማራችሁት ባህላዊ ልምዶች ማለት በቀደሙት ዓመታት ትውልድ እየተቀባበለ ያኖራቸው ልምዶች ማለት እንደሆን ተገንዝባችኋል፡፡ ለእኛና፣ ለሌሎች የሚጠቅመውን ብቻ ለይተን በእየለት ኑሮዎችን ልንተገብራቸው እንደሚገባ አውቀው ከሃገራቸው ባህል ጋር ጠንካራ ትስስር ሊኖራቸው ይገባል

# ምዕራፍ አምስት

## ጥመርታ ዝምድና እና ትግበራ

### መግቢያ

ጥመርታ ዝምድና እና ትግበራ (አተገባበር ) ስንል የፅሁፍ ወይንም የንግግር፤የእንቅስቃሴ ጥበብ እውቀትን ትክክለኛ እና ተስማሚ በሆነ መንገድ ወደ ተግባር የምንቀይርበት የአተገባበር ሂደት ነው፡፡




ተማሪዎች በዚህ ንዑሰ ርዕስ ውስጥም ሆነ ባለፉት ንዑሰ ርዕሶች ውስጥ የተማራችሁትን የክ.ዕ.ጥ ትምህርትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማገናኘት ከትምህርቱ ያገኛችኋቸውን መልካም ነገሮች በማዛመድ፣በማጣመር፣መተግባር መግለጽ እንድትችሉ ነው፡፡

ባህልን የአኗኗር ዘዴን፣እምነትን፣ ስነ ጥበብን፣ታሪክን ሃገር የሚያወደሱ መዝሙሮችን በቡድን እየዘመራችሁ እንድትማሩና እንድትረዱ፣እንድታውቁ ማድረግ እና በዚህ ክፍል ንዕስ ርዕስ ውስጥ የተማራችሁትን የክ.ዕ.ጥ.ን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማገናኝትና መተግበር እንድትችሉ ነው፡፡

ከዚህ ምዕራፍ በኋላ የሚጠበቅ የመማር ውጤት፡-

በዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች የሚከተለትን ትችላላችሁ፡፡

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ድምፆችን፣ሥዕሎችን፣ቀለሞችን ትለያላችሁ፡፡
- መዝሙሮችን በቡድን ትዘምራላችሁ፡፡
- በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ጥበባት ትረዳላችሁ፡፡
- የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ፡፡



## 5.1. የቡድን ዝማሬ

ከዚህ ንዑስ ርዕስ በኋላ የሚጠበቅ ዝርዝር የመማር ውጤት።

ከዚህ ንዑስ ርዕስ በኋላ የሚከተሉትን ትችላላችሁ።

- በአካባቢያችሁ የምትሰሙትን የዝማሬ ጥበብ ንግግር፣እንቅስቃሴን ትረዳላችሁ።
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ።
- በሃገራችሁ የሚገኙ ታሪኮችን ትረዳላችሁ።
- ዜማዎችን በማዳመጥ መልዕክቱን ትረዳላችሁ።
- ስለሃገራችሁ ያላችሁን ፍቅር ትጨምራላችሁ።
- ከአቻ ጓደኞቻችሁ ጋር በመከባበር በቡድን መዘመር ትችላላችሁ።
- የማንበብ ባህላችሁን ታዳብራላችሁ፤ታሳድጋላችሁ።

### አተገባበር ማለት ምን ማለት ነው?

አተገባበር ስንል የፅሁፍ ወይንም የንግግር፣የእንቅስቃሴ ጥበብ እውቀትን ትክክለኛ እና ተስማሚ በሆነ መንገድ ወደ ተግባር የምንቀይርበት የአተገባበር ሂደት ነው።የተማራችሁትን የዝማሬ ጥበብ ሀይልን የመዝሙሮችን መልዕክት በመረዳት

ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች እና ከሕይወታችሁ ጋር በማገናኘት እና በመማር የመተግበር ሂደትን የምታዳብሩበት የእይታና የክወና ጥበብ ነው፡፡

- በምስልና በድምጽ የተዘጋጀውን መዝሙር በመመልከት እና ታላላቆቻችሁን በመጠየቅ መልዕክቱን ወደ ተግባር ቀይራችሁ አስረዱ፡፡
- መጠመር ማጣመድ እና መተግበር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታላላቆቻችሁን በመጠየቅ ለመምህራችሁ ታስረዳላችሁ፡፡

መዝሙር 1.ሃገር የለኝም ከኢትዮጵያ ሌላ

ሻላላላ.....ሻላላላ ሻላላለ.....ሻላላ

ሀገር የለኝም......ከኢትጵያ ሌላ

እኔ አልፈልግም....ከሃገሬ ሌላ

ሻላላ....ሻላላ ሻላላ

ይገባቸዋል.....ካሁን በኋላ
ለኢትዮጵያ ልጆች...ብዙ አለ መላ



መዝሙር 2.ያገር ፍቅር ትዝታው



ያገር ፍቅር ትዝታው ትዝታው
አይረሳም ለሚያውቀው ለሚያውቀው (2 ጊዜ)

ያገሬ ተራራ ወንዛ ወንዙ ለምለም
ይናፍቃል ለዛው ትዝታው ሲታለም
ያገሬ ተራራ ወንዙ ሽንተረሩ

በጣም ይናፍቃል ተስማሚው አየሩ

ውብ ሀገሬ ውብ ሃገሬ ውብ ሀገሬ
ስትኖሪ ነው መከበሬ መከበሬ
-----------አዝማች-------






## መዝሙር 3. አበበ ቢቂላ

አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ለእነ ሺአለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረ ስላሴ፣ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ፣አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ ዓርአያ የነበረ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሯጭ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ እና ለአፍሪካ የመጀመሪያውን የዓለም ኦሎምፒክ ማራቶን እሩጫ ከዓለም ክብረ ወሰን ጋር ወርቅ ያስገኘ ኢትዮጵያዊ

ነው፡፡ በሮም ኦሎምፒክ ውድድር በባዶ እግሩ ሮጦ ያሸነፈ እትዮጵያዊ ጀግና ነው፡፡ የቶኪዮ ኦሎምፒክም የራሱን እና የዓለምን ክብረ ወሰን በማሻሻል ለሁለተኛ ጊዜ የወርቅ ሜዳሊያ በመሸለሙ በዓለም ታሪካዊ እና ዝነኛ ጥቁር ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

- ስለ ሻምበል አበበ ቢቂላ እና ሌሎች ስለምታውቋቸ ኢትዮጵያዊያን ሯጮች ታላላቆቻችሁን በመጠይቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አስረዱ፡፡



## አበበ ቢቂላ

አበበ ቢቂላ አበበ
አበበ ቢቂላ አበበ

ኦ....ሆ አ....ሃ አ.....ቤ

አቤ ብረቱ አልፍ ለናቱ
አቤ ብረቱ አልፍ ለናቱ
ጀቢራው ሳተናው ጀቢራው
ጀቢራው ሳተናው ጀቢራው
ያፍሪካ ሳተና ጀቢራው

አቤ ብላጠርታው ኢትዮጵያ እናቱ
አላሳፈራትም ባለ እግር ብረቱ
መሰረቱን ጥሏል ለሃይሌ ደራርቱ
መሰረቱን ጥሏል ለሃይሌ ደራርቱ




## መዝሙር 4.ማንበብ እወዳለሁ





## መዝሙር 4.ማንበብ እወዳለሁ

- ይህንን መዝሙር በጋራ ከዘመራችሁ በኋላ ለየብቻ በማጥናት እየተነሳችሁ ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ትዘምራላችሁ።
- የንባብ ጨዋታውን መምህራችሁን በማዳመጥ በመዘመር የማንበብ ባህላችሁን ታዳብራላችሁ።

ማንበብ እወዳለሁ ሁልጊዜ አነባለሁ
ባነበብኩኝ ቁጥር ይገባኛል ሚስጥር ...ሚስጥር....ሚስጥር
የጥበብን ሚስጥር የእውቀትን ሚስጥር
እኔ ልንገራችሁ በየመፅሐፍቱ ታገኙታላችሁ።



Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource



መልመጃ.1

1. የጎደለውን ግጥም በባዶ ቦታውን ሙሉ።

1. አቤ ብላ ጠርታው ኢትዮጵያ እናቱ
   አላሳፈራትም ባለ እግር ብረቱ
   መሰረቱን ጥሏል ---------- ------------

.2 ሀገር የለኝም ------------- ሌላ

   እኔ አልፈልግም ከሃገሬ ሌላ

## 5.2 በቡድን ውዝዋዜ

ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት


ይህንን ርዕስ ስታጠናቅቁ የሚከተሉትን ትችላላችሁ

- ከቡድን ተጣምራችሁ መወዛወዝ ትችላላችሁ
- የውዝዋዜ አተገባበር ትረዳላችሁ
- የዕርስ በርስ ግንኙነትን ታጠነክራላችሁ


### ውዝዋዜ እና ተፈጥሮ

በውዝዋዜ ተፈጥሮን መግለጽ እንደሚቻል ታውቃላችሁ ለምሳሌ የዛፎችን እንቅስቃሴ ስታዩት ንፋስ እየገፋው ወደግራ ወደቀኝ ሲነቃነቅ አስደሳች መልክ አለው።





የእንስሳትን ቡረቃ እና ጨዋታ ስታዩ የተፈጥሮ ስራ ደስ ይላል።





ውዝዋዜ ጥበብ ነው። በሀዘን፣በደስታ፣በስራ፣በአደን፣ ወዘተ... በውዝዋዜ ስሜታችሁን ትገልጻላችሁ።

## መልመጃ አንድ

የወፎችን ድምጽ እያስመሰላችሁ ንፋስ እንደመታው ዛፍ ወደግራ ወደቀኝ እየተወዛወዛችሁ ተጫወቱ እና እንዴት አስደሳች ጨዋታ እንደሆነ ተመልከቱ።

## መልመጃ ሁለት

እንደ እንስሳት ወዲያ ወዲህ እየፈነጠዛችሁ መጫወትን ተለማመዱ በእነዚህ ጨዋታዎች ተፈጥሮን ማድነቅ ትለምዳላችሁ

## 5.3 የሚና ጨዋታ በቡድን ውስጥ

**ከዚህ ርዕስ የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

ይህንን ርዕስ ስታጠናቅቁ የሚከተሉትን ትችላላችሁ

- ከቡድን ጋር ተባብሮ መስራት ትችላላችሁ
- ሚና ይዞ መጫወት ትችላላችሁ
- የዕርስ በርስ ግንኙነትን ታጠነክራላችሁ

ሚና ማለት ምን ማለት እንደሆን ባለፉት ምዕራፎች አይታቹሃል፡፡ የትወና ጨዋታ ደግሞ የተለያዩ ሚናዎችን በመከፋፈል የሚከወን መሆኑን ማወቅ አለባችሁ

**መልመጃ አንድ**

1. ቀጥሎ ያለውን ታሪክ በደንብ እዩት

አንዲት መምህርት፣ አንድ እንቅልፋም ተማሪ፣ አንድ የትምህርት ቤት ጥበቃ፣ እና አንዲት የምታሳዝን ተማሪ አሉ፡አስተማሪዋ ታስተምራለች፣ እንቅልፋሙ ልጅ ክፍል ውስጥ ተኝቶ በእንቅልፍ ልቡ ያወራል ፣ የምታሳዝነዋ ተማሪ ደሞ ፈርታለች፡፡

2. አሁን ደግሞ ሚና እየተከፋፈላችሁ ይህንን ድራማ ስሩ

መምህርት፡- ተማሪዎች በደንብ ተከታተሉ እሺ

ተማሪዋ፡- እሺ መምህርት እየተከታተልን ነው

መምህርት፡- በጣም ጥሩ፣ ጽዳት አስፈላጊ መሆኑን ተነጋግረናል.......

እንቅልፎ፡- (በትንሹ ድምጽ እያሰማ ይለፈልፋል) እ እ እ

መምህርት፡- እረፉ አልኩ እኮ. ማነው የሚለፈልፈው? ዋ!

ተማሪዋ፡- (ትደነግጣለች) እ እ እኔ አይደለሁም

መምህርት፡- በቃ! ማንም እንዳይረብሽ.... ወደ ትምህርታችን.. ጤናችንን ለመጠበቅ..

እንቅልፎ፡- (በትንሹ ድምጽ እያሰማ ይለፈልፋል) ህ ህ ህ

መምህርት፡- ተዉ አልኩ እኮ! አትሰሙም እንዴ? አሁን መቅጣት እጀምራለሁ

ተማሪዋ፡- እሺ መምህርት እንሰማልን

መምህርት፡- ጤንነትን ለመጠበቅ የግል ንጽህና አስፈላጊ ነው። ስለሆነም....

እንቅልፎ፡- (ጮክ ብሎ) ወይኔ ወይኔ ወይኔ እናቴ ነይልኝ

ተማሪዋ፡- ወይኔ ጉዴ ፈላ

መምህርት፡- ምን ሆነሃል

እንቅልፎ፡- ብስኩቴን በላብኝ

መምህርት፡- ማነው እሱ

እንቅልፎ፡- ይሄ አቡሌ ነዋ እናቴ የሰጠቺኝን ብስኩት በላብኝ ኡ ኡ ኡ ኡ

ጥበቃ፡- (በር በርግዶ ይገባል) ዘራፍ  ዘራፍ አከአኪ ዘራፍ እትትት ዘራፍ ወንዱ

መምህርት፡- አንተ ደግሞ ምን ሆነህ ነው

ጥበቃ፡ እትዬ  ቲቸር ማነው የደበደቦት ንገሩኝ ልርገጠው

ተማሪዋ፡- እሱ ነው እኮ የጮኸው

ጥበቃ፡ ምን ሆንክ ማን ደበደበህ?

ተማሪዋ፡- በ እንቅልፍ ልቡ ብስኩቱን ወስደውበት

ጥበቃ፡ እዚሁ ተኝቶ ንዋ

ተማሪዋ፡- አዎ

ጥበቃ፡- እኮ እክፍል ውስጥ

ተማሪዋ፡- አዎ

ጥበቃ፡- ሂ ወዲያ እንቅልፋም

መምህርት፡- በቃ የዛሬው ትምህርት አልቋል፡፡ ነገ ኑ፡፡ አንተ ግን እዚሁ ተኛ፣ እንቅልፋም

ከ በሀይሉ ዘለቀ 2013

### መልመጃ ሁለት

በቡድን በቡድን ከሆናችሁ በኋላ ለቡድናችሁ ስም ስጡ ወይም

ቡድን 1

ቡድን 2

ቡድን 3 እያላቹ ሰይሙ እና ሚና እየተቀያየራችሁ ከተወናችሁ በኋላ ዕርስ በርስ ተገማገሙ

## 5.4 የዕይታ ጥበብ ጥመርታና ትግበራ

| በስዕል ታሪካዊ ቦታዎችን ማመልከት |
|---|

ከዚህ ርዕስ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- በሀገራችን የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችን ታውቃላችሁ
- ታሪካዊ ቦታዎችን ማወቅ ያለውን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ
- ታሪካዊ ቦታን ማወቅ በዕይታጥበብ ያለውን ጠቀሜታ ታውቃላችሁ

መግቢያ

በስዕል ታሪካዊ ቦታዎችን ማመልከት

ተማሪዎች ታሪካዊ ቦታዎች ማለት ምንድነው?

ታሪካዊ ቦታዎች ጎብኝታችሁ ታውቃላችሀ?

የሰው ልጆች ከብዙ ሺህ አመታት በፊትም ሆነ ከአመታት በፊት የኖሩባቸው፣ታሪክ የሰሩባቸው የቀረጹዋቸው፣ፈልፍለው የሠሩዋቸው፣መስጊዶች፣ ቤተክርስቲያኖች ረዥም የእድሜ ዘመናትን ሲያስቆጥሩ ታሪካዊ ቦታዎች እንላቸዋለን፡፡


ታሪካዊ ቦታዎችን ማወቅ ብዙ ጥቅም ይሰጠናል

ለምሳሌ

1. በራሳችን የምንኮራና የሌሎችን የምናከብርና የምናደንቅ ህዝቦች እንሆናለን
2. የሀገራችን ታሪክና ሀብት ለመጠበቅ ይረዳናል
3. ታሪካዊ ቦታዎችን ለመጎብኘት ያነሳሳናል
4. ሀገራችን ለማወቅ ያግዘናል
5. ቱሪስቶች ወደ ሀገራችን እንዲመጡና ሀገራችን በሌላ አለም ለማስተዋወቅ ይጠቅመናል

## የታሪካዊ ቦታ ምስሎች

1. ላሊበላ ፡-



- በኢትዮጵያ በአማራ ክልል የቀድሞው ወሎ ክፍለ ሀገር የምትገኝ ከተማ ነች



የሰሜን ተራሮች

- በኢትዩጵያ በሰሜን ጎንደር የሚገኝ ሲሆን በሀገራችን ብቻ የሚገኙ የዋልያ፣ ቀይ ቀበሮ ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ ወዘተ ይገኙበታል

2. የአክሱም ሀውልት



- በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል በትግራይ ክልል የሚገኝ ረጅሙ ሀውልት ነው፡፡



3. የሐረር ጀጎል ግንብ በኢትዮጵያ ምስራቅ ክፍል የሚገኝ



4. የአጼ ፋሲለደስ ቤተ መንግስት



5. የኮንሶ መልክአ ምድር አቀማመጥ

- የጠንካራ አርሶ አደሮች የእርከንና እርሻ መልክአ ምድሩን ውበትን አላብሶታል::

የጥያ ትክል ድንጋይ

- በኢትዮጵያ በደቡብ/ ጉራጌ ዞን ላይ ጥያ ከተማ ላይ ይገኛል::

መልመጃ 1

የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ

1. በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ዝርያዎችን የያዘ ስፍራ የያዘ ስፍራ
   ሀ. አክሱም ሀውልት ለ. ሰሜን ተራሮች
   ሐ. የሀረር ግንብ መ. መልስ የለም
2. በኢትዮጵያ የሚገኙ ብዙ ስፍራዎች በዩኔስኮ በአለም ቅርስነት ተመዝገባዋል
   ሀ. እውነት ለ. ሐሰት

2.በሀገራችን ብቻ በሰሜን ተራሮች የሚገኙትን ምስሎች በመመልከት ድግማችሁ መሳል ተለማመዱ





ዋልያ　　　　　　ቀይ ቀበሮ

## የማጠቃለያ መልመጃ (ምዘና)

ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. መፅፍት በማንበብ ምን ምን እናገኛለን

   ሀ. እውቀት　　ለ. ጥበብን　　ሐ. ሁሉም መልስ ነው፡፡

2. ውብ ሀገሬ ውብ ሃገሬ ውብ ሀገሬ-------------------መከበሬ መከበሬ

   ሀ. ባንች እኮ ነው　　ለ. ስትኖሪ ነው　　ሐ.ትዝታው

3 .በኢትዮጵያ በአማራ ክልል የሚገኝ ታሪካዊ ቦታ የትኛው ነው

   ሀ. ላሊበላለ/አክሱም　　ሐ. የሀረር ግንብ

4 .በኢትዮጵያ በመልከአ ምድር አቀማመጡና በቅርስነት የተመዘገበው-------------ነው

ሀ/ የኮንሶ መልአምድር ለ/ የፋሲለደስ

ሐ/ የጥያ ትክል ድንጋይ መ/ መልስ የለም

## ማጠቃለያ

አተገባበር የፅሁፍ ወይንም የንግግር ፤የእንቅስቃሴ ጥበብን እውቀትን፤ ያወቅነውን ነገር ወደ ተግባር የምንቀይርበት መንገድ ነው፡፡ በመዝሙር፤ በእንቅስቃሴ፤በምስል ስሜታችንን እና ሐሳባችንን መግለጽ እንደሚቻል አይታቹሃል፡፡የክወናና እና የእይታ ጥበብ ደግሞ በሁሉም የሰው ልጅ ሂወት ውስጥ እንደሚኖር ግልጽ ነው፡ ፡ስለዚህ አንዱን ካንዱ አየነጠሉ ከማየት በማጣመር የሚተገበር ጥበባዊ ስራ ነው፡፡

በተጨማሪም የቡድን ስራ ውስጥ የተለያዩ ሰዎች ይኖራሉ በዚህ መሰረት አንዱ ካንዱ ሃሳብ፣ችሎታ እና ሌሎችም መልካም ነገሮችን እየተወራረሱ አስቸጋሪ ነገሮች ሲከሰቱ እየተመካከሩ መስራት በጣም ጥሩ ነገር መሆኑን ተገንዘቡ

# ዋቢ መፅሃፎች

1. ናስሪን ዚገ፡፡ ደንሺ ሳሮን ደንሺ እና ሌሎች የህጻናት ታሪኮች፤ የጀርመን የባህል ተቋም ፤ 2006
2. የ 4ኛ ክፍል የኤስተቲክስ መማሪያ መጽሃፍ፤የአ.አ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ 1998
3. የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ አ.አ.ዩ የካቲት 1993

Fetena.net : Ethiopian No#1 Educational Resource

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም / 2022 /